

የደርቤ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

ዋጋው አንድ ብር

# ትንሣኤ



ቅዱስ ጊዮርጊስ ሊቀ ሰማዕታት

ቁጥር ፹፮

ኅዳር ፲፱፻፸፯ ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶ ዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እም ነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማ ትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተ ግባር ጭምር እንዲተረጉሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »

አዘጋጅ
ልሣነወርቅ በዛብኅ ፤
ም ከነፈ ርግብ ማርቆስ


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

# ማውጫ

**አርእስት** **ገጽ**

ደብዳቤዎች ...... ፩
ብፁዓን ገባርየነ ሰላም የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው ...... ፪
ቅድስት ሐና የድንግል ማርያም እናት ...... ፬
ታሪክ አይደበቅም ...... ፮
ዜና ሊቃውንት ...... ፱
ልማት በቤተ ክርስቲያን ...... ፲፩
ቅዱስ ጊዮርጊስ ሊቀ ሰማዕታት ...... ፲፪
ተጠርቶ ተላከ ...... ፲፬
ታቦተ ጽዮን (ጽላተ ሙሴ) ...... ፲፭
መርቆሬዎስ ሰማዕት ...... ፲፮
የመንፈስ ቅዱስ ልዩ ልዩ ሀብታት ...... ፲፰
የወ/ት ሳባ ታደሰና የአቶ ሚ ባባከር ድራሜ ጋብቻ በጸሎተ ተክሊል ተፈጸመ ...... ፳
የቤተ ሰብ ዓምድ (ከብቸኛነት ወደ ቤተ ሰብነት) ...... ፳፩
ዜና ዕረፍት የአቶ ምትኩ ለማ አጭር የሕይወት ታሪክ ...... ፳፪
የጤና ዓምድ የእናቶችና የሕፃናት ጤና አጠበባቅ ...... ፳፫




ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ ፦

በመጀመሪያ የአብ ጸጋ የወልድ ቸር ነት የመንፈስ ቅዱስ አንድነት ከሁላ ችን ጋር እንዲሆን እየተመኘሁ ጤና ይስጥልኝ እላለሁ ።

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ኦርቶዶ ክር ቤተ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያና ችንን ታሪክና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን ጥሬ ቃላቶች በማብራራት እንዲሁም የመላእክትን የጻድቃንንና የሰማዕታትን በእግዚአብሔር ኃይል ተአምር አድራጊነት በማብራራት ታት ሞ በየወሩ በመውጣቱ ምእመናን በደ ስታ እየተከታተሉ ያለ አስተማሪ የሚ ፈልጉትን ትምህርት በመመገብ ላይ ይገኛሉ ።

ስለሆነም ይህ መንፈሳዊ ተግባር መቋ ረጥ ሳይኖርበት ሊቃውንቱ በሕይወት እስከኖሩ ድረስ በትጋትና በንቃት በመሥራት ሥራው እየቀጠለና እየተ ስፋፋ እንዲሄድ በትሕትና አሳስባለሁ ።

ከዚሁ ቀጥየ ለእኔም ሆነ ለሌሎች ምእመናን ግልጽ እንዲሆን የሚከተሉ ትን ጥያቄዎች አቀርባለሁ ።

፩ኛ/ በዚህ ዓለም የሚኖር ሰው የተለ ያየ መልክ ያለው መሆኑ ግልጽ ነው ይኸውም ነጭና ቀይ ጥቁር እየተባለ ከመጠራቱም በላይ መልኩ ምስክር ነው የመጀመሪያዎቹም አዳምና ሔዋን ናቸው ነገር ግን እነዚህ የመጀመሪያ ዎቹ ሰዎች ይህንን ሁሉ ሕብረ መል ክዕ አጠቃለው ይዘው ነበርን ?

፪ኛ/ ሰዎች እንደመልካቸው ፀጉራ ቸው የተለያየ ሆኖ ይታያል ይኸውም ሉጫ ፤ ከርዳዳ ወዘተ ነው ታዲያ ከሁ ለቱ ሰዎች ከአዳምና ሔዋን የማናቸው ጠጉር ነበር ሉጫ ? ወይም ከርዳዳ ?

፫ኛ/ በዘፍጥረት ምዕ. ፮. ፩ - ፭ ሰዎች በምድር ላይ በበዙጊዜ ሴቶች እንደ ተወለዱ ይጠቅስና የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ልጆች ለትዳር እንደወሰዱ ይና ገራል የእግዚአብሔር ልጆችና የሰው ልጆች የተባሉት እነማን ናቸው ?

፬ኛ/ በዚሁ ምዕ. ፮ - ፯ እግዚአብሔር ሰውን በምድር በመፍጠሩ ያዘነ መሆ ኑንና በቁጣውም ያጠፋቸው መሆኑን ይገልጸል ነገር ግን ኢአማናውያንየሆኑ አምላክ ነው ትላላችሁ ሁሉን ማወቅ ሲገባውና ሰው ከጥፋት የማይመለስ መሆኑን ካወቀ ለምን በመፍጠሩ ተፀፀ ተ ? ለምንስ በንፍር ውሀ እንስሳትን ጭምር አጠፋ ? እንስሳት ምን አድርገ ዋል ?

ቀጥሎም ከዚህ በማያያዝ ግብፃው ያን በእስራኤላውያን ላይ ከባድ ግፍ ያደረሱባቸው በመሆናቸው ከዚሁ አሠራራቸው እንዲመለሱ በሙሴ አማ ካይነት የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ቢተ ላለፍላቸውም አልተቀበሉም ፈርዖን ልበ ደንዳና በመሆኑ ሕዝቡም የእርሱ ን መንገድ በመከተል ልበ ደንዳና ሆነ በዚህም ምክንያት በባሕረ ኤርትራ ውስጥ ተሰጠሙ ነገር ግን ጥፋቱ የሰ ዎች ሲሆን ፈረሶች ምን በድለው ነው ከሰዎች ጋር የተሰጠሙት ?

ስለዚህ ይህን ያደረገ አምላክ አይደ ለም በማለት ተጠራጥረው ሌሎችን ስለሚያጠራጥሩ ይኸው ጥያቄ በትን ሣኤ መጽሔት ታትሞ ወጥቶ ለአንባ ብያን እንዲሠራጭ በትሕትና እጠይ ቃለሁ ።

ሰላመ እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን

መ.ተ.ደ.

ሲዳሞ ክ/ ሀገር
ጀምጀም አውራጃ
ቦሬ ከተማ

መልስ

ጠያቂው ስላቀረቡልን መንፈሳዊ ሰላምታ እያመሰግን ላቀረቧቸው ጥያቄ ዎች መልስ እንሰጣለን ፤

በዚህ ዓለም ቀይና ነጭ ጥቁር ወዘተ መልኮች መኖራቸውን ገልጸው የአዳ ምና የሔዋን መልክ ምን ዓይነት እንደ ነበር እንዲገለጽልዎ ጠይቀዋል ፦

አዳምና ሔዋን የተፈጠሩት ከነፋስ ከእሳት ከመሬት ከውሀነው፡ስለዚህየእሳ ትመልኩቀይ ሲሆንየነፋስአርዓያጥቁ ር ነው እንዲሁም የውሀ ባሕርይ ነጭ መሆኑ ሲታወቅ የመሬት ባሕርይ ደግሞ ቢጫ መሆኑ ይነገራል ሁለቱ አዳምና ሔዋንም ከተጠቀሱት ፬ቱ ባሕርያተ ሥጋ የተፈጠሩ ስለሆኑ ይህንን ሕብ ረ መልክዕ ብቻ ነው ይዘው የተፈጠ ሩት ብሎ ቅዱስ መጽሐፍ አልነገረንም ስለዚህ ጥቁሮች ወይም ነጮች ናቸው ብለን ለመናገር አንችልም በጠጉራቸ ውም በኩል የቀረበው ቃለ መጠይቅ በዚሁ መልስ ሊጠቃለል ይችላል ።

በመጽሐፈ ሄኖክ ተጽፎ እንደሚገ ኘው ነጭና ቀይ ሰው መውለድ የተጀ መረው በ፲ኛውትውልድ ነው በ፩ሺ፮፻ ፶፮ ዓ.ዓ. ኖኅ ሲወለድ ፀዓዳ ሁኖ ስለተ ወለደ አባቱ ላሜህ በጣም ደነገጠና ወደ አባቱ ማቱሳላ ሂዶ ንጣቱ በረድ የሚመስል ዓይኑም ጠጉሩም ነጭ የሆነ ልጅ ቢወለድ የመልአክ ልጅ ነው መስ ሎኝ ደንግጬ ልነግርህ መጣሁ ቢለው አባቱ ማቱሳላ መልሶ መልአክስ አይ ደለም ሰው ነው ብሎ ወደፊት የሚሠራ ለት ታሪክ ተገልጾለት በትንቢት አስ ረድቶት ተመልሷል መጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ ፹፩. ፩ - በግዕዙ ወእምድረ መዋዕል ነሥአ ወልድየ ማቱሳላ ለወ ልደ ላሜህ ወፀንሠት እም ኔሁ ወወለ ደት ወልደ ወኮነ ሥጋሁ ፀዓዳ ከመ አስሐትያ ወቀይሕ ከመ ጽጌ ረዳ ወጸ ጉረ ርእሱ ከመ ፀምር ፀዓዳ ተብሎ ተጽ ፏል ይህ ንባብ የነጭ ሰው መጀመሪያ ኖህ መሆኑን ያስረዳል እንዲሁም ከጥ

ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# ብፁዓን ገባርየነ ሰላም የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው

ማንኛውም ሰው በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠረ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዱናል ተፈጥሮውም ከቶቱ ባሕርያት ነው ፡ እነርሱም እሳት ፡ ነፋስ ፡ ውሀና መሬት ናቸው ። ስለዚህም የመናደድና የመ ቸኮል ባሕርያት ሲኖሩት በዚያው አንፃር ደግሞ የመታገሥ ባሕርይ አለው ።

በተናደደና በተበሳጨ ጊዜ አስተምረው መክረው እንዲታገሥ አድርገው ትክክለኛውንና ቀናውን መን ገድ በመራመድ የዚህን ዓለም ኑሮ በሰላም እንዲያሳልፍ የሚያደርጉ መካሮች ያስፈልጉታል ሰው ሆኖ የማይበ ድል እንጨት ሆኖ የማይጨስ አይገኝምና ሰው በልቡ አስቦ በአፉ ተናግሮ የተፈጥሮ ወገኑንም ሆነ ፈጣሪውን ሊበድል ይችላል ። ጊዜ እንሚያሥቶት ቢበድልም በዚያው ጥፋቱ እንዳይጨምርበት ባለፈው በደሉ ተጸጽቶ ለወ ደፊቱ ለመጠንቀቅ እንዲችል አስታራቂዎች ያስፈላጉታል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራ ላይ ካስተማራቸው ዘጠኝ የብፅዕና ቃላቶች አንዱ የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና ይላል የማቴ. ወን ፭. ፱ በዕርግጥ ደከመኝ ታከ ተኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ጉልበታቸውን ሳይቆጥቡ ሰውን ከሰው ጋር የሚያስታርቁ መምህራንም ሆኑ ሽማግሌዎች ቀድሞም ነበሩ ዛሬም መኖራቸው አይካድም ።

በድሮ ዘመን እነ መልከ ጼዴቅ እነ ሊቀ ሀገር እንደነበሩ በታሪክ እንረዳለን መልከ ጼዴቅ የተባለው ደግ ና ሰላማዊ ሰው ሰዎች ሲጣሉ የሚያስታርቅ በሐሠት ተጣልተውና ተካሰው ሲከራከሩ እውነት የማፈርድ ስለ ነበር የሰላም ንጉሥ እየተባለ ይጠራ ነበር ሊቀ ሀገርም የተባለው ሰው ሦስት ልጆች ነበሩት ማልዶ ተነሥቶ እነ ርሱን አንተ በዚህ ዋል አንተ ደግሞ ይህንን ሥራ ብሎ በየሥራቸው አሠማርቶ እርሱ የተጣላ ወዴት አለ ? እያለ እየጠየቀ የተጣሉትን ሰዎች ሲያስታርቅ ይውል ነበር ዕብራ ፯. ፩ - ፫

ሰውን ከሰው ጋር ማስታረቅ ብቻ ሳይሆን ሰውን ከእግዚአብሔር እግዚአብሔርን ከሰው ጋር ማስታረ ቅም የተቀደሰ ተግባር መሆኑን ማወቅ ያስፈል... ። የሰው ልጅ ሠርቆ ቀምቶ ከፈጣሪውና ከተፈጥሮ ወገኑ ጋር የሚጣላው የሚበላውና የሚጠጣው የሚለብሰው ቢያጣ አይደለምን ብለው የሚበላውና የሚጠጣው የሚለብ ሰውም በመስጠት ሰውን ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር የሚያስታርቁ ብፁዓን ንዑዳን ክቡራን ናቸው ።

እንዲሁም የማይገባ ሥራ በመሥራት ከፈጣሪው የራቀውን ሰው በትምህርተ ወንጌል አለዝበው በን ስሐ አድሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቁ መምህራንና ቀሳውስት ቁጥራቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባ ላሉ ተብለው ከተነገረላቸው ገባርያነ ሰላም ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መስቀል ወጥቶ ወደመቃብር ወርዶ ለሰው ልጆች ሰላምን እንደሰጠ አቀበቱን ወጥተው ቁልቁለቱን ወርደው የተጣሉትን አስታርቀው የተፀዱሉትን አስክሰው የተቀ ሙትን አስመልሰው በሰዎችና በሰዎች መካከል ያለውን ጥላቻ በማስወገድ ሰላምንና ፍቅርን የሚመሠርቱ በእውነት የክርስቶስ ተከታዮች ናቸውና በእግዚአ ብሔርም ሆነ በሰው ዘንድ ከፍ ያለ ዋጋ አላቸው ።

ጥንቱንም ቢሆን የሰው ልጅ የተፈጠረው ሕግን ጠብቆ በሰላም እንዲኖር ነበር ከተፈጠረም በኋላ የተሰ ጠችው ቦታ ምድረ ገነት ነበረች ከዚያች ቦታ ሰላም የሰፈነ ነበር ፡ እንስሳት አራዊት ሳይቀሩ እርስ በእርሳቸው መጣላትን አያውቁም ነበር ሁሉም ተስማምተው በሰላም ይኖሩ ነበርና ነገር ግን እግዚአብሔር አምላክ አንድ ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር ያ ያስተላለፈው ትእዛዝ ባይጠበቅ ሰላምና ፍቅር ተወግደው ጥል እንደሚመሠረት ተና ግሮ ነበር ግን የሰው ልጅ የተሰጠውን መመሪያ ባለመጠበቁ ሰላማዊ ኑሮው ወደ ጥላቻ አስደሳችሕይወቱ ወደ አሳዛኝ ነገር ተለውጦ እርሱ ብቻ ሳይሆን እንስሳትና አራዊትም ኀርስ በእርሳቸው ተስማምተው ለመኖር አል ቻሉም ።

አዳም በገዛ እጁ ያስነጠቀውን ሰላም በቶሎ መልሶ ለማግኘት አልቻለም በሰዎችና በእግዚአብሔር መካ ከል የጥል ግድግዳ ቆመ ይህንን የጥል ግድግዳ አፍርሶ ፍጹም ሰላምን ለመመሥረት የሚችል ባለመገኘቱና



ሁሉም መናገር እንጂ ሰላምን ለማምጣት ስለተሳነው አስታራቂ በማጣት ሰውና እግዚአብሔር ተራርቀው አያ ሌ ዘመናት ኑረዋል ።

ብዙ ነቢያት በየጊዜው እየተነሡ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል የተጋረደው የጥል ግድግዳ ፈርሶ ጥላቻ ተወግዶ ፍጹም ሰላም የሚመሠረትበትን ዘመን ከመናገር በስተቀር በትንቢታዊ ቃላቸውና በሥልጣና ቸው የጥልን ግድግዳ አፍርሰው እግዚአብሔርንና ሰውን ለማስታረቅ አልቻሉም ነበር ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህዓለም መጥቶ ከድንግልማርያም በተወለደጊዜ ግን የሰላም ጭላንጭልመ ታየት ጀምሯል በክርስቶስ ልደት የፈነጠቀው የሰላም ጮራ፡በመስቀሉና ሞትን በሞቱ በመደምሰሱ ዓለሙ በጠቅላላ የሰላም ገለቤት ለመሆን በቅቷል ።

ሐዋርያው ጳውሎስ በክርስቶስ አስታራቂነት የተገኘውን ሰላም ሲገልጽ "በዚህ ዓለም ተስፋን አጥታ ችሁ ከእግዚአብሔር ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክር ስቶስ ኢየሱስ ሁናችሁ በደሙ ቀርባችኋል እርሱም ሰላማችን ነውና ሁለቱን ያዋሀደ በዓዋጅ የተነገሩትንም ፡ የት እዛዛት ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳ በሥጋው ያፈረሰ ፡ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁላቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ ሰላምን ቀርበው ለነበሩትም የምሥራች ብሎ ሰበከ ሲል መልእክቱን ለኤፌሶን ሰዎች አስተላልፎአል ኤፌ. ፪ ፡ ፲፬ - ፲፯

፳፻ ህ ፳፻ ዘመን ሙሉ ከፈጣሪው ርቆ ከክብር ተራቁቶ በፍዳና በመከራ የኖረውን የሰው ልጅ በመስ ቀሉ ያስታረቀው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሁንም በሰው ልጆች መካከል ጠብና ክርክር ምቀኝነትና ጥላቻ እርስ በእርስም መለያየት እንዳይኖር ይፈልጋል ።

በደመ መስቀሉ ያዳነው የሰው ልጅ በክርስቶስ ደም ያገኘውን ሰላም ሊጠቀምበት ይገባዋል ሰው በሕ ይወተ ሥጋው ከተፈጥሮ ወገኖቹ ጋር በሰላም የሚኖርበትን በሕይወተ ነፍሱም ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሚ ሆንበትን ቀና መንገድ ይዞ መራመድ ይገባዋል ።

በዚህ ዓለም ላይ አሁን ለሰው ልጅ ከፍተኛች ችግሮች ናቸው ተብለው ከሚገመቱት መካከል ታላቁን ነጥብ ይዞ የሚገኘው የሰላም ዋስትና ማጣት ነው አንዱ ሀገር በሌላው ሀገር ላይ ሰላም የሚደፈርስበትን ፍቅር የሚጠፋበትን መንገድ ይከተላል እንዲሁም ሌላው በአፉ የሰላም ወሬን እያስተጋባ በልቡ የተንኮል ገመድን ይገምዳል ።

ከመራቀቁና ከመፈላሰፉ ጋር አብሮ እያደገ የሚሄደው የጥፋቱ መሣሪያም የዚያኑ ያህል ነው ሰላምን በዓለም ላይ ለማስፈን የሚጥሩ ፡ አስታራቂዎች መኖራቸው ባይካድም ጥረታቸው ተሳክቶ አስተማማኝና ዋስትና ያለው ሰላምን ለመመሥረት ባለመቻላቸው የዓለም ሕዝብ ከሥጋት ነፃ ሊሆን አልቻለም ።

" እባብ ለእባብ ይታያያሉ ካብለካብ" እንደሚባለው አንዱ በሌላው ላይ የጥፋት ዱላውን ለመሰንዘር አመች የሆነ ጊዜን ሲጠብቅ ሌላው ደግሞ በበኩሉ የሚሠነዝርበትን የጥፋት ዱላ በማክሸፍ መልሶ ለመደብደብ መሣሪያውን ያዘጋጃል ።

ሥጋዊንም ሆነ መንፈሳዊን ሕይወት በትክክለኛው መንገድ ለመምራት ከሰላም የበለጠ መሣሪያ በዚህ ዓለም ላይ ሊገኝ አይችልም ሰላም በዓለም ሰላም በሀገር ፣ ሰላም በጐረቤት ሰላም በቤት እንዲሰፍን መጣር የሁ ሉም ሰው ዓላማ ሊሆን ይገባል ።

ሰላም ራሱ ከሰዎች ፊት ሊሸሽ አይችልም ሊያባርሩትና ሊያሸሹት የሚችሉት የሰው ልጆች በክፉ ሥራ ቸው ነው የተለያዩትን አንድ የሚያደርጉ ፣ የተጣሉትን የሚያስታርቁ ፡ የተራራቁትን የሚያቀራርቡ እውነተ ኞች የሆኑ አስታራቂዎች በዚህ ዓለም ላይ ተፈላጊዎች ናቸው "ሰውን ከሰው ጋር የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና ተብሎ እንደተጻፈው ሽማግሌዎች እንዲያስታርቁ ጠበኞች እንዲታረቁ ። የሰው ዘርም በጠቅላላ በሰላም ፡ በፍቅር በአንድነት በመረዳዳት ለመኖር እንዲችሉ ሁሉን ማድረግ የማይሳነው ፈጣሪ ዓለሙን ሁሉ በቸርነቱ ይጐብኘልን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ቅድስት ሐና የድንግል ማርያም እናት

ሐና ማለት ሐይማኖቷ የቀና ምግባሯ ያማረ የተባረከች መልክ ከደም ግባት ያላት ማለት ነው የቅድስት ሐና አባቷ ማጣት እናቷ ሄርሜላ ትባላለች ሁለቱም ማጣትና ሄርሜላ ልጅ ሳይወልዱ መክነው ይኖሩ ነበር ነገር ግን ለልባቸው ተስፋ ለዓይናቸው ማረፊያ ልጅ እንዲሰጣቸው አዘውትረው ፈጣሪያቸውን ይለምኑ ነበር ።

ከዕለታት አንድ ቀን ሰምዖን የሚባል ደግ ሰው ወደሄርሜላ ሄዶ"ወይን በማኅፀንሽ ገብታ ለምልማ አፍርታ ፍሬዋን ዓለሙ ሁሉ ሲመገበው አይቻለሁና ደስ ይበልሽ"ብሎ ነገራት፡ እርሷም የእግዚአብሔር ፈቃዱ ይሁን ብላ የምስራቹን በደስታ ተቀበለችው ።

ከዚያም ቀን ጀምሮ ማጣትና ሄርሜላ አንድ ሱባኤ ወደ እግዚአብሔር ተማለሉና በሱባኤያቸው መጨረሻ ላይ ሁለቱም አንድ የደረቀ ወይራ ዛፍ ከቤታቸው አጥር ወድቆ የሚኖር ለምለሞ በሦስት ክፍል አፍርቶ ለሁለቱም ሲሰጣቸው አዩ በዚህም ሲደነቁስለዋኖስየሚባል ሽማግሌ ከጐረቤታቸው ይኖር ነበር ያ ሽማግሌ ስለእነርሱ ሕልም አይቶ ሊነግራቸው መጣና አልጋችሁ ለምልሞ አበባ ሲያብብ አበባውም ሲያፈራ ዛሬ ሌሊትበሕልሜአይቼ ልነግራችሁመጣሁ አላቸውእነርሱምአባታችን እንደቃልህ ይደረግልን ብለው በደስታ አነጋገረው በሰላም ሸኙተው ሰደዱት ።

ከዚያም በኋላ መልአኩ ቅዱስ ራጉኤል ተገልጾ እግዚአብሔር ጸሎታችሁንና ምጽዋታችሁን ተቀብሎ እንደምኞታችሁ የተባረከች ደግ ልጅ ከእናንተ እንድትወለድ ፈቃዱ ሆኖአል ብሎ ነግሯቸው ወደ ሰማይ ሲያርግ ታያቸው ሄርሜላና ማጣትም ይህንን አስደሳች ዜና ከመላኩ በመስማታቸው ከፍ ያለ ምስጋና ለእግዚአብሔር አቀረቡ ወዲያው ብዙ ሳይቆይ በ፳፫ ፴፫፭ ዓ.ዓታኅሣሥ ፲፰ ቀን በዘመነ ማቴዎስ በዕለተ ስሉስ ሄርሜላ ፀነሰች መፅነሷም በዘመዶቿና በአካባቢዋ ተሰማ ።

ማኑሄ የሚባል አንድ ጋኔን የሚጥለው ሰው ነበር አንድ ቀን ሄርሜላ ከቆመችበት አጠገብ ሄዶ ቆሞ ሳለ ጥላዋ ቢያርፍበት ዋይ ብሎ በኃይል ጮኸና ወደቀ ይህንን ጩኸቱን ሰምተው ሰዎች ቢጠይቁት በዚህች በሄርሜላ ማኅፀን ያለችሕፃንእንደእሳትአቃጠለችኝና ወደቅሁ አሁንም በእርሷ አምላክ እምናለሁ ሁለተኛ ከዚህ ሰው አልደርስም ብሎ ምሎ ሰው ሁሉ እያየው በዝንጀሮ መልክ ተመስሎ ከሰውየው ተለይቶ እንደአሞራ ሲበርታየ። ይህንንም ያዩ ሰዎች እጅግ በጣም ገርሟቸው ከዚህች ሴት ከቶ እንደምን ያለች ፍጥረት ትወለድ ይሆን እያሉ እያደነቁ የመወለጃዋን ጊዜ በናፍቆት ይጠባበቁ ጀመር ።

ዳግመኛ ልያ የምትባል ሴት በኢየሩሳሌም ትኖር ነበር ይህችም ሴት በሆዷ የተፀነሰው ዕንስ አጥንት ሆኖ ሆዷን እየወጋ ጤና አሳጥቷት በችግር ትኖር ነበር በዚህ ጊዜ ሄርሜላ በሆዷ ፅንስ ጋኔን እንዳወጣች ሰምታ እኔንም ከዚህ በሽታየ ብታድነኝ ብላ ወደሄርሜላ ሄደችና ሆዷን ዳሳ በሕማም የሚያሰቃያትን የሆዷን አጥንት እሽት እሽት ብታደርገው ፴ት ዓመት ሙሉ አጥንት ሆኖ የኖረው ዕንስ ወደ ሕያውነት ተለውጦ ተወለደ ይህም ሕፃን ታሪኩ ብዙ በሚል ስም ሲጠራ እንደኖረ በገድለ ሃና ተጽፏል ።

በሄርሜላ ማኅፀን የተፀነሰው ፅንስ ሴትን ይሁን ወንድ እስከሚወለድድረስ ያወቀ አልነበረም ከ፱ ወር በኋላ በ፳ሽህ ፴፫፭ ዓ.ዓ. ከ፱ ወር መስከረም ፯ ቀን በዘመነ ማርቆስ በዕለተ ሐሙስ ሄርሜላ ሴት ልጅ ወለደች በዚህም ዕለት ወላጆቿ ከፍ ያለ በዓል አድርገው ዘመድ አዝማዳቸውን ወዳጆቻቸውን ሲቀበሉ ዋሉ ልዩ ልዩ ደቁም የያዛቸው ሄርሜላ የወለደችበትን መሬት እየዳሰሱና እየተቀቡ ከበሽታው ተፈውሰዋል ። በተወለደች በ፹ ቀን ሥርዓተ ግዝረት ሲፈጸም ስሟን ሐና ብለው አወጡላት ።

ሐና ማለትም ከላይ እንደተገለጸው ሃይማኖቷ የቀና ምግባሯ የሠመረ የተባረከች መልኳም እጅግ በጣም ያማረ ማለት ነው ሐናም ቀስ በቀስ አድጋ ፫ ዓመት ሲሆናት ወላጆቿ ሕርማኖስ ከሚባል መምህር የኦሪትን ትምህርት እንዲያስተምራት አስገቧት በሰባት ዓመት ውስጥ የኦሪትን ትምህርትና ሥርዓተ ረበናትን በጠቅላላ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከእናትና አባቷ ሕግ ጋር አጠናቃ ተማረች ።

ቅድስት ሐና ፲፭ ዓመት ሲሆናት ከቤተ ይሁዳ የቅስራን ልጅ ኢያቄምን አገባች ኢያቄምም እንደ እርሷ የተማረ ነበርና ሁለቱም እግዚአብሔር የሚወደውን በኦሪት የተጻፈውን ሕግ ሁሉ በሚገባ የሚጠብቁ ፈጣሪያቸውን የሚፈሩ ለድኃ የሚያዝኑና የሚራሩ ጾምን ጸሎትን የሚያዘወትሩ ደጋግ ሰዎች ሆኑ ።

ሀብታቸው ግን በመጠን ነበር እንጅ ብዙ ሀብት እንደዘመዶቻቸው አልነበራቸውም በእንደዚህ ያለ ቅድስና ፈጣሪያቸውን እያገለገሉ ሲኖሩ ስማቸውን የሚያስጠራ የዓይናቸው ማረፊያ የልባቸው ተስፋ የሚሆን ልጅ ሳይወልዱ መክነው በመኖራቸው ኃያሉ እግዚአብሔርን ልጅ ይሰጣቸው ዘንድ ተስፋ ባለመቁረጥ በመዓልትም በሌሊትም እያለቀሱ ይለምኑት ነበር፣

እግዚአብሔር ግን የወዳጆቹን የሃይማኖት ጽንዓት ለመፈተን ልጅ እንዳይወልዱ ጸሎታቸውን የማይቀበል መስሎ ለብዙ ጊዜ የሐናን ማኅፀን ዘጋ ከዕለታት አንድ ቀን ሐና ከጐረቤቷ አንዲት በዝሙት አዳሪ ሴት ነበረችና እህቴ ሆይ፣ ቤተ እግዚአብሔር ደርሼ ልመጣ ነበር ግን ይህ ልብሴ ያደፈ ነው ንጹሕልብስ ባገኝ ያንን ለብሸ ሄጀ እግዚአብሔርን ለምኘ እመጣ ነበር አለቻት ያችም ሴት፣ ጐረቤት በእንዲህ ያለችግር ለመረዳዳት ነው ፣ አሁንም ከእኔ ብዙ ልብስ አለልሽ ፣ የፈለግሽውን አንዱን ለብሰሽ ልትሄጅ ትችያለሽ አለቻት ሐናም ነገሩ መልካም ነበር ነገር ግን ይህ ልብስሽ በአሰበ ዶነስ የተሰበሰበ እንደሆነ ይህንን ለብሶ ወደ ቤተ እግዚአብሔር መሄድ አይገባም እግዚአብሔር ንጹሐ ባሕርይ ስለሆነ የሚወደው ንጹሕ ነገርን ነው አለቻት ።

ይችም ሴት በጣም ተናደደችና ሐና እኔ ለአንች ልጅ በማጣትሽ አዝንልሽ ነበር ለካ በዚህ ክፋትሽ ነው እንደ እንጨት አድርቆ ያስቀረሽ ብላ ሰድባ ሰደደቻት ሐናም እያዘነች ያኑ የነበራትን ልብስ ለብሳ ሂዳ መሪር የሆነ ልቅሶ አልቅሳ ተማሕፀንዋንም አቅርባ ወደቤቷ ስትመለስርግብወልዳከልጆቿ ጋርስትጫወት አይታ ጌታዬ ሆይ ለዚህች ግዕዛን ለሌላት እንስሳ ልጅ ስትሰጥእኔን ድንጋይ ሁኝ ድንጋይ ነሽ ብለህ ፈጥረኸኛልን እባክህን ፈጣሪዬ አምላኬ ሆይ ለማንም መዘባበቻና መሣለቂያ አታድርገኝ ብላ ምርር ብላ እያለቀሰች ከቤቷ ገባች ።

የገጠማትንም ሁሉ ለባሏ ለኢያቄም ነገረችው በዚያችም ሌሊት ሁለቱ እንደ ተተከለ ምሰሶ ቁመው ልጅ ይሰጣቸው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልዩ አደሩ ጧት ሐና ኢያቄምን እስኪ ፈጣሪያችን ጸሎታችን ቢቀበለን መባ ይዘን ስእለት ተስለን እንመጣ ዘንድ ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንሂድ አለችው እርሱም እሽ ብሎ መባቸውን ይዘው ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሄዱ ከዚያም ሲደርሱ መባቸውን ለዕቃ ቤቱ ጠባቂና ስለት ተቀባዩ ሮቤል አቀረቡ ሮቤልም እግዚአብሔር ብዙ ተባዙ ውለዱ ተዋለዱ ብሎ ከመረቃቸው መካኖች ተለይተው የተረገሙ ስለሆኑ እናንተም መካኖች ናችሁና መባችሁን አልቀበልም መልሳችሁ ውሰዱ አላቸው ።

እነርሱም እያዘኑና እያለቀሱ ጌታችን ፈጣሪያችን ሆይ ልቅሶአችን ተመልከተህ ወንድ ልጅ የሰጠኸን እንደሆን አርሶ ቆፍሮ እኛን ይረዳን አንልም ለቤተ እግዚአብሔር አገልጋይ እንዲሆን እና ደርጋለን ሴት ልጅም ብትሰጠን እንጨት ለቅማ ውሀ ቀድታ ወፍጮ ፈጭታ እንጀራ ጋግራ ትረዳን አንልም መጋረጃ በመፍተል መሰበ ወርቅ በመስፋት ቤተ እግዚአብሔርን እንድታገለግል እናደርጋለን ብቻ ለዓይናችን ማረፊያ ለልባችን ተስፋ የሚሆን አንድ ልጅ ስጠን ብለው ተሳሉ ።



ሐናና ኢያቄም ይህንን የህሊና ጸሎትና ብፅዓት በቤተ እግዚአብሔር አድረገው ሲፈጽሙ ወደ ሊቀ ካህናት ዘካርያስ ሂደው መምህራችንና አባታችን ሆይ እኛ መካኖች መሆናችንን ታውቃለህ ወደፊት ፈጣሪያችን ወንድም ሆነ ሴት ልጅ ቢሰጠን ለቤተ እግዚአብሔር መብዓ አድርገን እንሰጣለን እንጂ እኛን ያገልግለን ታገልግለን አንልም ብለን ተስለናልና ይህ ስዕለታችንም እንዲፈጸምልን እግዚአብሔርን ለምንልን የመሰነባበቻም ቡራኬ አድርግልን ብለው ከእግሩ በታች ወደቁ ።

ዘካርያስም እግዚአብሔር ጸሎታችሁን ይስማችሁ ስእለታችሁንም ይፈጽምላችሁ ልቅሶና ኀዘናችሁን ይመልከትላችሁ ብሎ በመጸለይ አሰናበታቸው ኢያቄምና ሐና ወደቤታቸው ተመልሰው በጾም በጸሎት እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ጥቂት ጊዜ እንደ ቆዩ በ፳ሺ ፴፭፻፹፫ ዓ.ዓ. በዘመነ ማርቆስ በዕለተ እሁድ ነሐሴ 7 ቀን ሐና ከባሏ ከኢያቄም ፀነሰች ፡- ከ፯ ወር በኋላ መጽነሷ ስለታወቀ ዘመዶቿ ወደእርሷ እየመጡ ከአረጀች በኋላ በመፅነሷ እየተጠራጠሩ ሆዷን እየዳሰሱ ይረዱ ነበር ።

ከሐና ከዘመዶቿ ወገን አንድ አይና አክስት ነበረቻት ሆዷን ዳስሳ ዓይኗን ብትነካው እንደሁለተኛው ደኅና ሁኖላታል ። ይህንን ዜና የሰሙ ዕውራን አንካሶን እንዲሁም በልዩ ልዩ ደዌ ተይዘው የሚሠቃዩ ሁሉ ማኅፀኗን እየዳሰሱ የሚፈወሱ ሁነዋል ጸላዕያን ሠናያት አይሁድ ይህንን ሰምተው በማኅፀን ሳለ እንደዚህ የሚፈወስ በተወለደ ጊዜ ምን ተአምር ይሠራ ይሆን ብለው በጣም ፈሩ ተንቀጠቀጡ ከፍርሃታቸውም የተነሣ ተሰበሰቡና በደንጊያ





www.ethiopianorthodox.org

ወግረን በእሳት አቃጥለን እንግደላቸው ብለው ተማክረው ሳሉ በመንፈቀ ሌሊት ቅዱስ ገብርኤል ወደ ሐናና ኢያቄም መጥቶ ተነሡና ተከተሉኝ ብሎ እየመራ ወደ አድባረ ሊባኖስ ወሰዳቸው ፦ በዚሁም ተራራ በ፭ሺ ፬፻፺፬ ዓ.ዓ ከዘጠኝ ወር በዘመነ ሉቃስ በዕለተ ስሉስ ግንቦት ፩ ቀን ቅድስት ሐና እንደ ፀሐይ የምታበራ እንደ አንበሳ የምታስፈራ መልኳ በጣም የምታምር ልጅ ወለደች ።

በዚህ ጊዜ ከአድባረ ሊባኖስ ጀምሮ በኢየሩሳሌም ዙሪያ ብርሃን ሲወርድ ታየ እስከ ፯ ቀንም ብርሃኑ አልጠፋም ነበር አባትና እናቷም ፯ ቀን ሙሉ ከዘመዶቻቸው ከወዳጆቻቸው ጋር ደስታ አደረጉ ሐና ከወለደችበት ቦታ ዙሪያ ለተአምራት ከአራት ቦታ ላይ ውሀ ፈለቀ ሕፃኗ በተወለደች በ፹ ቀን ስሟን ማርያም ብለው ሠየሟት ።

ስለምን ማርያም አሏት ቢሉ በዚህ ዓለም ሰዎች ከሚመገቡት ምግብ ሁሉ ለአፍ የሚጥመው ለልብ ደስ የሚያሰኝና ልብን የሚመስጥ ማር ነው በገነት የሚገኙ ጻድቃን ከሚመገቡት ምግብ ጻድቃንን ቅዱሳንን በጣዕም ደስ የሚያሰኛቸው በገነት ውስጥ በጣፋጭነት ብልጫ ያለው ያም የሚባል ምግብ ነው ስለዚህ ከሁሉ የበለጥሽ ነሽ ሲሉ ማርያም አሏት ።

ይህችም ቡርክት ማርያም ከሐና ከመወለዷ በፊት ገና በሆዷ ሳለች ሙት አስነስታለች ይኸውም ሳሚና የሚባል የየጦሊቅ ልጅ ከኤዶቅ ከአጐቱ ቤት ሂዶ ሞተ ዘመዶቹም ለመቅበር በአልጋ ላይ አድርገው ይዘውት ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሲጓዙ የሐና የአጐቷ ልጅ ስለነበር በጣምትወደውነበርናእስከሬኑ ያለበትን አልጋ እየዞረች ስታለቅስ ጥላዋ ቢያርፍበት ተነሥቶ ስብሐት ለኪ እሙ ለፀሐየጽድቅ፡ማርያምሆይ!የአብ ሙሽራው ለወልድ ወላዲቱ ለመንፈስ ቅዱስ ጽርሐ ቤቱ ደስ ይበልሽ ብሎ ሰገደላት ቤተ አይሁድም ከዚያው ከልቅሶው ነበሩና ምነው ምን አይተህ ነው ለዚህች ለሐና የሰገድከው አሉት ።

ሳምና-ስም እኔ የሰገድኩት ከዚህች ከሐና ማኅፀንየምትወለደውሕፃንሰማይንና ምድርን ባሕርና የብስን እመቀ እመቃትን አየረ አየራትን ወዘተ የፈጠረ

አምላክን ትወልዳለች እያሉ መላእክት ሁሉ ሲያመሰግኗት ሰምቼ ነው እኔንም ያስነሣችኝ እርሷው ናት ብሎ ተናግሮ ተመልሶ አርፏል ።

ይህም ድንግል ማርያም ከተወለደች በኋላ ብዙ ተአምራት እንደምታደርግ የሚያመለክት ነበር ኢያቄምና ሐናም ይህንን የመሰለ ተአምራት ስለተመለከቱ ለሰሚ ደስ የሚያሰኝ ስም አውጥተው ውላታል ለቤተ እግዚአብሔርም የሚገባ መባ አዘጋጅተው ወስደው ቢያቀርቡ በፊት አንቀበላችሁም ብለዋቸው የነበሩት ሁሉ በክብርና በደስታ ተቀበሏቸው ከዚያ በኋላ በተወለደች በሦስት ዓመቷ ድንግል ማርያምን ወስደው በዚያን ጊዜ የቤተ እግዚአብሔር ሐላፊ ለነበረው ለሊቀ ካህናቱ ለዘካርያስ አስረከበውታል በስዕለት የተወለደች ናትና ድንግል ማርያም በወላጆቿ ቤት ፫ ዓመት በቤተ መቅደስ ፲፪ ዓመት ከኖረች በኋላ የዓለም መድኃኒት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሣ በድንግልና ወልዳለች እርሱም በደመ መስቀሉ ዓለሙን ሁሉ በጠቅላላ አድኗል ።

በታሪኩ እንደተመለከትነው ሐናና ኢያቄም አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት ይበቃል በተባለው መሠረት በሕግ ተወስነው በትዕግሥ እግዚአብሔር ፀንተው በመኖራቸው ፣ ምክንያተ መሠረተ ሕይወት የሆነችውን ድንግል ማርያምን ለመውለድ በቁ አሁንም ቢሆን በሕግ ተወስነው በትዕግሥ እግዚአብሔር ጸንተው በጸሎት በጾም ፈጣሪያቸውን የሚለምኑ ሰዎች ከራሳቸው አልፎ ለሀገር ለወገን የሚጠቅም ፈጣሪውን የሚፈራና የሚያከብር ልጅ ለማግኘት ይችላሉ ።

ክቡር ዳዊት "ልቡናቸው ርኁሩኅ ለሆኑ ሰዎች እግዚአብሔር ቅርብ ነው ብሎ እንደተናገረው እምነቱን አጠንክሮ ሥነ ምግባሩን አሳምሮ ፈጣሪውን የሚለምን ሁሉ እንደኢያቄምና ሐና የለመነውን ያገኛል ለምኑ ይሰጣችኋል ፈልጉ ታገኛላችሁ ደጅ እንኳኩ ይከፈትላችኋል ሲል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሮናልና ።

አባ ገ/ መስቀል ተስፋ ዘገነተ ማርያም



# ታሪክ አይደበቅም

እውነተኛ ታሪክና በተራራ ላይ የምታበራ ብርሃን አንድ ናቸው ፣ ይህንን ለማለት የፈለግሁት በተራራ ላይ የምታበራ ብርሃን ወይም መብራት ለማንም ፍጡር ልትደበቅ እንደማትችል ሁሉ እንዲሁም እውነተኛ ታሪክም ከእውነተኛው ማኅደረ ታሪክ ሊደበቅ አይችልም ።

ይህም ሲባል ያለምክንያት አይደለም ሊዳሰስና ሊጨበጥ የሚችል ዓቢይ ተግባር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አንፃር ከመቼውም ጊዜ ጐልቶ በመታየቱ ነው ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊትና ታሪካዊት እንደመሆኗ እናት ቤተ ክርስቲያን ፣ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ፣ የሚለውን ታሪካዊ ስም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማትረፍ በቅታለች ፣ ከመነሻው ላይ ታሪክ አይደበቅም የተባለውም ስለዚህ ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዚህ አንፃር ከመቼውም ጊዜ ይልቅ በአሁኑ ወቅት የዓለም አቀፋዊነትን ክብር በመጐናጸፍ ላይ ናት ለዚሁም ምስክሩ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፊት መንበረ ክብሯን ይዛ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጐን በመሰለፍ ከዚህ ቀደም ያደረገችው መንፈሳዊ አስተዋጽኦና አሁንም በማበርከት ላይ በምትገኘው ተመሳሳይ ተግባር በመሆኑ ለማንም የተሠወረ አይደለም ።

በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላትን የቀረበ ግንኙነትና ወዳጅነት በተግባር መተርጐምና የበኩሏንም ምግባረ ሠናይ በማበርከት ላይ ትገኛለች ፣ እንዲሁም የዓለም አብያተ ክርስቲያናትም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋር በአላቸው መልካም ግንኙነትና ወዳጅነት መሠረት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ ።

ለዚሁ ሁሉ ማሠሪያ አንቀጹ ግን ሊደበቅ የማይችለው ገድለ ታሪኳ በመሆኑ ለታሪካውያን ዓውደ ምሥጢር ነው በይበልጥ በአሁኑ ክፍለ ዘመን የአብያተ ክርስቲያናት መቀራረብ የሰላምና የትክክለኛ ፍትሕ ትርጉም ለማይገባቸው ብሎም ዓይነ ልቡናቸው በአፓርታይዝ በሽታ የታወረባቸውን መንግሥታት በአንድነት ለማውገዝ አመች ሁኔታ ለመፍጠር መቻሉ ግልጽ ነው ።

ከዚህ ሌላ ለዓለም ሕብረተሰብ ጠንቅ የሆነው የጦር መሣሪያ እንዳይስፋፋ ከሚያወግዙት አብያተ ክርስቲያናት አንዷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በመሆኗ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ለኢትዮጵያውያን ምእመናን ሁሉ ከፍተኛ የሆነ የታሪክ ምዕራፍ ነው ።

በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያን ምድራዊት የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ መሆኗ መጠን ለምድራውያን ፍጥረታት ሁሉ ኃላፊነት እንዳለባት ሊዘነጋ አይገባም ፣ ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሰማይ ላለው ፍጡርም ሰላም ይገባዋል በማለት እግዚአብሔር አምላክ በፍጥረቱ ወይም በሕብረተሰቡ እንዲመሰገን ፣ ሕብረተሰቡም በእግዚአብሔር አምላክ ሰላምን ፍቅርን እንዲያገኝ ከመጸለይ ተቆጥባ አታውቅም ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር ተባብራ ከመሥራቷ የተነሳ ወዳጅነቷን እያጠነከረች በመሄድ ላይ ትገኛለች በዚህም ሁኔታ ከውጭ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር የቤተ ክርስቲያናችን ግንኙነት እየጠነከረ ከመሄዱም ሌላ ታሪካዊትና ጥንታዊት መሆኗን የተረዱ የውጭ የታሪክ ሰዎች (ማዘር ቸርች) እናት ቤተ ክርስቲያን እያሉ ይጠሯታል ።

በእውነቱ ይህ የሚገባ አጠራርና አከባበር እንጂ ለይስሙላ የተሰጠ አጠራርና አከባበር አለመሆኑ እንዲታወቅ ያስፈልጋል ምክንያቱም ታሪክ እንደ ሌሊት አውሬ በጉድጓድ ውስጥ ተደብቆ ለመኖር ባለመቻሉ ነው ። በዚሁም ይዘት መንፈሳዊ አስተያየቷ ከብሔራዊ ድርጅት ወደ ዓለም አቀፍ ደረጃነት በመሸጋገሩ ቤተ ክርስቲያናችን ለሌላው ክፍለ ዓለም ከማስተዋወቁ ሌላ የአንድነትና የወዳጅነትን በር ለመክፈት በመቻሉ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሁሉ ደስ ሊሰኙ ይገባቸዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ገብተው በመማር ነባራዊውን ትምህርት ከሐዲሱ የፍልስፍና ትምህርት ጋር በማነፃፀር የነገረ መለኮትን ጥልቀትና ምጥቀት በመመርመር ከመጨረሻው ግብ ይደርሳሉ ተብሎ ባይገመትም በሚያደርጉት ጥናት ትንሽ ጨላጨል ለመመልከት መቻል እንዳለባቸው መካድ የለበትም ።

የቤተ ክርስቲያን አባቶች የነገረ መለኮትን ጥልቀትና ምጥቀት በሙሉ ለማወቅ የማይችሉ መሆናቸውን ሲያረጋግጡ የውቅያኖስን ውሃ በጭልፋ እንደ መቅዳት ያህል ነው ይላሉ በዚህ አንፃር ለማወቅ የሚያስፈልግ ቢኖር ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት የሚሰጠው እስኮላር ሽፕ ለማን እንደሚሰጥና ለምንስ እንደሚሰጥ ለመገንዘብ አስቸጋሪ ነው ተብሎ ባይገመትም ቅሉ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት በቀጥታ እስኮላር ሽፕ የሚሰጡት በግለሰብ ደረጃ ሳይሆን ለታሪካዊቱ እናት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናችን መሆኑን ለመጠቆም እንፈልጋለን ። ወዳጅ አብያተ ክርስቲያናት እስኮላርሽፕ ለምን ይሰጣሉ ? ለተባ



www.ethiopianorthodox.org

ለው ቃል ደግሞ ጥንታዊትነቷንና ታሪካዊትነቷን በማመን ከእርሷ ጋር ወዳጅነትንና ግንኙነትን ለማጠንከር መሆኑ እሙን ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ከወዳጅ አብያተ ክርስቲያናት የምታገኘውን የነፃ ትምህርት ዕጋ ለልጆቿና ፡ ለአገልጋዮቿ ፡ ታድላለች ፡ ከዚህ ቀደሞም አድላለችአሁንምበማደል ላይ ትገኛለች ወደፊትም እንደምታድል ተስፋ አለን ይህም ለቤተ ክርስቲያን ልጆች ትልቅ የደስታ ብሥራት ነው ።

ከዚህ ላይ ወደሌላ ሐተታ ሳንሄድ ሊደበቅ የማይችለውን እውነተኛውን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከተገነዘቡት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መካከል ።

፩ኛ/ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፡

፪ኛ/ የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ፡

፫ኛ/ የሩማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይገኙበታል ።

እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የነፃ ትምህርት ከሚሰጡት ሌሎች ክፍሎች ቅድሚያን የያዙ ናቸው የተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት ለቤተ ክርስቲያናችን ባለውለታዎች ናቸው ቢባሉ ከእውነት የራቀ አይሆንም ይህ ሁሉ በታሪኳ ላይ የተመረኮዘ ነው ።

ለምሳሌ የፀሐይን ብርሃን ደመና ሊከልለው ይችላል እንዲሁም የሚነፍሱትንም ነፍሳት ተራራ ሊጋርዳቸው ይችል ይሆናል ፡ ታሪክን ግን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ሥነ ፍጥረታት ሁሉ ሊጋርዱት አይችሉም ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ብሩህና ወርቃማ ታሪክ ነው ። ይህንን አስመልክተው የውጭ ጸሐፍት ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሲጽፉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በእስያና በአፍሪካ በሚገኙ ቤተ መቅደሶች ሁሉ ቅድሚያን የያዘች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያናት ብለዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከእስያና ከአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ከአውሮፓውያንም አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ በላይ መሆኗ አይጠረጠርም ፣ የዛሬው ታሪክ የትናትናውን ታሪክ ካላስታወሰ የዛሬው ታሪክ ከምን ላይ እንደተመሠረተና ከየት እንደተነሣ ለመገንዘብ አዳጋች ይሆናል ምክንያቱም ለአሁኑ ታሪክ መነሻውና መድረሻው ያለፈው ታሪክ ነውና፣

ለዚሁም ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል ብንመለከተው በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ በብዛት ተጽፎ እናገኘዋለን እዚህ የኢትዮጲያ ቤተ ክርስቲያን ሂደት በታሪክ ሊቃውንት አንፃር ምን ያህል ተቀባይነት እንዳለው ለማወቅ አያዳግተንም ።

ቀ. ኢያሱ ገብሬ



# ዜና ሊቃውንት

በዚህ የዜና ሊቃውንት ዓምዳችን እያዘጋጀን የምናቀርበው ለቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ አገልግሎት አበርክተው ያለፉትንና አሁንም በማበርከት ላይ የሚገኙትን የጉባኤ መምህራን የህይወት ታሪክ መሆኑን ደጋግመን መግለጻችን የሚታወስ ነው ።



መምህር ጌጡ ተሰማ በጉባኤ ላይ

በዚሁ መሠረት በዛሬው ጽሑፋችን ለአንባብያን የምናቀርበው በሕይወተ ሥጋ በማስተማር ላይ የሚገኙትን የመምህር ጌጡ ተሰማን የሕይወት ታሪክ ይሆናል ።

መምህር ጌጡ ተሰማ በ፲፰፻ህ፱፻፮ ዓ.ም. ከአባታቸው ከመሪጌታ ተሰማ ውቤና ከእናታቸው ወ/ሮ የተመኙ እሸቴ ጋይንት አውራጃ ስማዳ ወረዳ ደብረ ዕንቁ ማርያም ተወለዱ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ወላጅ አባታቸው የድጓ መምህር ስለነበሩ ቤታቸውን ሳይለቁ ከዚያው ከአባታቸው ፊደል ጀምረው እስከ ድጓ ድረስ ፀዋትወ ዜማን አጠናቀው ተማሩ ።

ከዚህ በኋላ በ፲፱፻፳፫ ዓ/ም ወደ ጐጃም ክፍለ ሀገር ሄደው ብቸና አውራጃ ደብረ ብርሃን ቅዱስ ጊዮርጊስ ከነበሩት ስመ ጥሩና ዝነኛ ከሆኑት መምህር ውብሸት እንግዳ ቅኔ ከእነአገባቡና ከእነዕርባ ቅምሩ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ ።

በተጨማሪም መምህር ጌጡ ተሰማ ከእኚሁ መምህር ነገሥት ፣ የውዳሴ ማርያምና የቅዳሴ ማርያም የመዝሙረ ዳዊት ትርጓሜን ፣ የበዓላትና የአጿማት ማውጫ የሆነውን ባሕረ አሳብ በሚገባ አጠናቀው ተምረዋል የተጠቀሱትን የትምህርት ዓይነቶች ተምረው ከፈጸሙ በኋላ በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ወደትውልድ ሀገራቸው ተመልሰው የቅኔ ትምህርታቸውን ማስተማር ጀምረዋል ። ለጥቂት ጊዜ ካስተማሩ በኋላ ጉባኤያቸውን ሳይፈቱ እያስተማሩ በመማር ዕውቀትን ለመጨመር ሲሉ ደብረ ታቦር አውራጃ እስቴ ወረዳ ወደም ትገኘው ስመ ጥሩ ደብር ማኅደረ ማርያም ሂደው ከመምህር ክፍሌ ወ/ጻድቅ አቋቋም ተምረዋል ።

መምህር ጌጡ ተሰማ የአቋቋም ትምህርታቸውን ተምረው ወደቦታቸው ከተመለሱ በኋላ ጉባኤያቸውን በሚገባ አስፍተው በንቃትና በትጋት አስተምረው ብዙ ምሁራንን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል ። ሊቁ ማስተማር ከጀመሩ እንሥቶ እስከ አሁን ፵፱ ዓመታት ናቸው በእነዚህ ዓመታት ፲፭ ወንበር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው የሚያስተምሩ መምህራንን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሲያበረክቱ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ቀሳውስትንና ዲያቆናትን እንዲሁም መዘምራንን በማስተማር ለቤተ ክርስቲያናችን ከፍ ያለ ውለታ ውለዋል ። ከእርሳቸውም የተማሩ ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል ላይ ይገኛሉ ።

መምህር ጌጡ ተሰማ "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት" ባለው አምላካዊ ቃል መሠረት ወ/ሮ አንጓች ይታየውን በሥርዓተ ተክሊል አግብተው ሦስት ወንዶች ሦስት ሴቶች በድምሩ ፮ ልጆችን ወልደው ለቁም ነገር አብቅተዋል፡ በመብረቅ ተቃጥላ ለብዙ ዘመን ሳትሠራ በመቃኞ የኖረችውን ደብረ ዕንቁ



www.ethiopianorthodox.org

ማርያምን ሕዝበ ክርስቲያኑን በማስተባበርና ከመንግሥትም ርዳታ በመጠየቅ በሚገባ አሳንፀው ጣራዋንም ቆርቆሮ እንዲከደን አድርገዋል ። የደብሯም አስተዳዳሪ መምህረ ደብረ ዕንቁ እንዲባል አድርገው እርሳቸው የመጀመሪያው አስተዳዳሪ በመሆን ተሹመው ከማስተማሩ ጋር ሲያስተዳድሩ ለብዙ ዘመን ኑረዋል ።

መምህር ጌጡ ተሰማ ከ፲፱፻፳፯ ዓ.ም ወዲህ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በማኅደረ ስብሐት ልደታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቅጽረ ግቢ ቦታ ተሰጥቷቸው በማስተማር ላይ ይገኛሉ ።

አሁን ስለአሉበት ሁኔታና ወደፊት ስላላቸው ዓላማ እንዲያብራሩልን መምህሩን ጠይቀናቸው የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተውናል ። እንደሀገር ቤቱ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ደቀ መዛሙርት ባይገኙም ቀን ሥራቸውን ሲሠሩ እየዋሉ ማታ ማታ እየመጡ የሚማሩ ፲፭ ተማሪዎች አሉኝ ስለዚህ በማንኛውም ጊዜ ግሥ ሳልገሥ ቅኔ ሳልዘርፍ አድሬአላውቅም ። ወደፊትም ቢሆን እርሱ ፈጣሪዬ እስከፈቀደልኝ ድረስ ማስተማሬን አላቋርጥም ብለዋል ።

በተጨማሪም ፊደል ንባብ ዳዊት የሚማሩ ፵ በላይ የሚሆኑ ልጆች ያሉ መሆናቸውን ገልጠው በቤተ ክርስቲያንም አገልግሎት በኩል ሌሊት በሰዓታትና በማኅሌት ቀን በስብከተ ወንጌል ቤተ ክርስቲያንን ነቅተው እንደሚያገለግሉ ተናግረዋል ።

ምን ችግር እንዳለባቸውም ጠይቀናቸው መምህር ጌጡ ሲገልጹ በአሁኑ ጊዜ ችግር የለብኝም አንዳንድም ችግር ቢደርስብኝ እግዚአብሔር አምላክ እንዳስቻለኝ እችለዋለሁ ብለዋል ። መምህር ጌጡ አሳባቸውን ለማጠቃለል ሲቃረቡ እኔ በአሁኑ ጊዜ የምደሰተው ያስተማርኩኝ ሳይመስለኝ ያስተማርኳቸውን የመንፈስ ቅዱስ ልጆቼን በሄድኩበት ቦታ ሁሉ በማግኘቴ ነው ።

በአሳቡ መጨረሻ ላይ የማኅደረ ስብሐት ልደታ መጉባኤ ለኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት እንክብካቤ እየተደረገልኝ ኢየሩሳሌም ሄጄ ተሳልሜ እንድመለስ በሚገባ ጽፎልኝ ይኸው ጉዳይ ስለተፈጸመልኝ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው በማለት ማብራሪያቸውን አጠቃለዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ድሃ አይደለችም እንደ መምህር ጌጡ ተሰማ በቅን መንፈስ ደቀ መዛሙርቱን እያስተማሩ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚያቀርቡ አያሌ ሊቃውንት አሏት ።

ነገር ግን ከጥቂቶቹ በስተቀር ለአብዛኞቹ መምህራን እንክብካቤ ስለማይደረግላቸው በልዩ ልዩ ፈተና ላይ እየወደቁ ናቸው ። አንዳንዶቹ ወንበር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው ብዙ ተማሮችን ሰብስበው ሲያስተምሩ የወረርሽኝ በሽታ በገባባቸው ጊዜ የሕክምና ርዳታ ስለማይደረግላቸው በበሽታው ምክንያት የሞቀውና የደመቀው ጉባኤያቸው ይፈታል ።

ሌሎች መምህራን ደግሞ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ እያጡ ይቸገራሉ ፤ አንዳንድ ጊዜ ከተማሮች መምህራኑ የሚቸገሩበት ጊዜ አለ ስለዚህ መምህራንም ሆኑ ደቀ መዛሙርቱ እንዳይቸገሩ በየቤተ ክርስቲያኑ አጥቢያ የተቋቋመው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የመንከባከብ ግዴታ አለበት ።

ስለዚህም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በሁለተኛው አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ መምህራን ካላስተማሩ ተማሮች ካልተማሩ በቤተ ክርስቲያን ላይ ከባድ ችግር ይደርሳል ችግሩ ግን የሚታወቀው አሁን ሳይሆን በሚቀጥለው ትውልድ ሊሆን ይችላል በማለት አስገንዝበዋል ።

አሁንም መላልሰን የምናስገነዝበው የቤተ ክርስቲያን አባል የሆኑ ሕዝበ ክርስቲያኖች ሁሉ አቅማቸው በሚፈቅድላቸው መጠን መምህራንንም ሆነ ተማሮችን መርዳትና መንከባከብ እንዳለባቸው ነው ።

መምህራንም በበኩላቸው እንደታላቁና ዝነኛው ሊቅ መምህር ጌጡ ተሰማ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በንቃትና በትጋት ደቀ መዛሙርቶችን አስተምረው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማቅረብ ይገባቸዋል ።

መምህር ጌጡ ተሰማም ከአሁን ቀደም በቅን መንፈስ ስላበረከቱት መንፈሳዊ አገልግሎት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እያመሰገነች በገቡት ቃል ኪዳን መሠረት እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ለመቀጠል እንዲችሉ እግዚአብሔር አምላክ ኃይሉንና ብርታቱን እንዲሰጣቸው ትመኝላቸዋለች ።

የዜናው አቅራቢ ቄስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ



መ/ጌጡ ተሰማ



# ልማት በቤተ ክርስቲያን

እንደሚታወቀው ባሁኑ ጊዜ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሥራዬ ብላ ከተነሣችበትና ሐሳቧን ከጣለችበት ልዩ ልዩ ልማቶችን የምታካሂድባቸው ስብከተ ወንጌልን የምታስፋፋባቸው ጊዜያት አሁን ነው ።

ይኸውም ቤተ ክርስተቲያን ራስዋን በራስዋ እንድትረዳ በተሰጣት መብት መሠረት ሰፊ ሜዳ ተዘርግቶላት ቀናው መንገድ ተቀይሶላት በመታየቱ ነው ይህንንም የመሰለ መብት በማግኘትዋ እነሆ በየቦታውና በየቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ ተፈላጊዎች የሆኑትን ልማቶች በማካሄድ ላይ ትገኛለች ።

ምሳሌም ቢያስፈልግ እንደነ ምስካየ ሕዙናን መድኃኔ ዓለም የመሳሰሉት በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ግቢ ውስጥ መንፈሳዊት/ቤት በማቋቋም በዚያ አካባቢ የሚገኙትን ሕፃናት ሰብሰባው ዘመናዊውንና መንፈሳዊውን ትምህርት ሁለቱን አጣምሮ በማስተማር ሀገራቸውን የሚወዱና የሚጠቅሙ እናት አባታቸውን የሚያከብሩ ወገንንና ዘመድን በመንፈሳዊ ተግባራቸው የሚያኮሩ ዜጎችን በማፍራት ላይ ይገኛሉ ።

ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም ቢሆኑ ምንም እንኳ እንደ ምስካየ ሕዙናን መድኃኔ ዓለም ሰፊ ድርጅት ባይኖራቸውም በአካባቢያቸው ከሚገኙ በጎ አድራጊዎችና አንዳንድ ደጋግ ምእመናን በስለት በተገኘው ገንዘብ ቤተ ክርስቲያን ገቢ የምታገኝበትንና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችም የሚረዱበትና የሥራቸውንም ፍሬ የሚያገኙበትን በማስብ ንጹሕ ቃለ ወንጌልን ለማስራጨትና ትምህርት ባልደረሰበትም ቦታ ትምህርትን ለማዳረስ ተሸጠው የሚረዱ ስጋጃ ፣ ሻንጣ ቦርሳ ሻማ የመሳሰሉትን የእጅ ሥራዎችን ከፍተኛ ልማቶችን በማስፋፋት ላይ ይገኛሉ ።

አዎ የዚህ ዓይነት ልማት በሀገራችን በኢትዮጵያ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ቢካሄዱና ከልማቱ የሚገኘውም ገንዘብ እየተቆጣጠረ በተገቢ ቦታ ቢውል ኑሮ ድኃ ቤተክርስቲያንና የሰውን እጅ የሚመለከት ቄስ በኢትዮጵያ ባልተገኘም ነበር ግን እንዲህ ባለማድረግ የጨናማ ለማኝ ሁና እናያታለን ።

የቤተ ክርስቲያን ልማት በየክፍለ ሀገሩና በየአውራጃው በየወረዳውና በየቀበሌው ተቋቁሞ ቢስፋፋ ካህናቱና ዲያቆናቱ የሰውን እጅ ከማየት ከማዳኑና ከማላቀቁም በላይ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን እርዱኝ በማለት እርዳታን ለመቀበል እጅዋን ከማንሳት ይልቅ ራስዋን ችላ ራሳቸውን መርዳት ላልቻሉ ለመርዳት እጇዋን በዘረጋች ነበር ።

ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን ልማት በአብዛኛዎቹ ካህናት እንግዳመስሎበመታየቱና ካለመታወቁ የተነሳ ካህናቱ ዲያቆናቱ የሰውን እጅ ሲመለከቱ እንጂ እነሱ ድኃውን ሲረዱ የተቸገረውን ሲያጽናኑና ችግሩን አስወግደው ከችግሩ ሲያላቅቁ አይታዩም ።

በእውነቱ የኢትዮጵያ ካህናት ዲያቆናት እንደ ብዛታቸው መጠን /መኑ ዘይተክል ወይነ ወኢየበልዕ ፍሬሁ ወመኑ ዘየሐቀብ ላህመ ወኢይሰቲ ሀሊቦ "ወይንን ተክሎ ፍሬውን የማይበላ ላምን ጠብቆ ወተትን የማይጠጣ ማን ነው" ፩ኛ ቆሮ ፱ - ፯ እያሉ ቢያስተምሩና ቢያሉበት አብያተ ክርስተቲያናት ቢተጉ ሌሎችን ለመርዳት በቻሉ ነበር ።

ነገር ግን ምን ይሆናል ቄሱም ገዝም መጽሐፉም ገዝም እንደሚባለው እነሆ አንዳንድ ካህናት ለመስጠት ሳይሆን ለመቀበል እጃቸውን ሲዘረጉ ይታያሉ እርግጥ በኢትዮጵያ ያሉ ካህናትና ዲያቆናት በአንድ ወገን በሬ ጠምደው እርፍን ጨብጠው ቤተ ሰቦቻቸውን ሲያስተዳድሩ በሌላ ወገን ደግሞ ጠባለኪዳን መሸለቁርባን እያሉ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ስለሚሠሩ ድርብ ሥራ እንደሚሠሩ የሚካድ አይደለም ።

ይሁን እንጂ ይህ ጽሑፍ የሚያመለክተው አንዳንድ የሰለጠኑ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች በተሾሙባቸው አድባራት /አብያተ ክርስቲያናት/ አካባቢ ልዩ ልዩ ልማቶችን እያቋቋሙ ቤተ ክርስቲያኑን እንደሚያሻሽሉ ሁሉ ሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ይህንን ፈለግ በመከተል ዓይናቸውን ቢከፍቱና በመጠኑ ልማትን ቢያቋቁሙ እንዴት ባመረና በተወደደ ነበር ማለታችን ነው ።

እረ ለመሆኑ ቤተ ክርስቲያናችን በውጭ ሀገር በእርዳታ የሚመጣውን ገንዘብ ተስፋ አድርጋ የምትኖረውና በዚያው ዓይኗን አተኩራ የምትኖረው እስከ መቼ ድረስ ነው ።

የውጭ ሀገር አብያተ ክርስቲያናትም ቢሆኑ እኮ እኛን ሲረዱንና እጃቸውን ሲዘረጉልን የሚኖሩት ራሳቸው ሳንቲሙን ቀጥቅጠው ወረቀቱን ብር አትመው አይደለም ገቢ የሚገኝበትን ልማት በማልማትና ካለሙትም ልማት የተገኘው ነው ችግረኞችን የሚረዱበት ፤

እንግዲያስ በውጭ ሀገር የሚገኙት አብያተ ክርሳቲያናት በተለያየ ዘዴ የገንዘብ ገቢ አግኝተው ራሳቸውን ችለው ራሳቸውን ላልቻሉ ኋላ ቀር አብያተ ክርስቲያናት የሚረዱ ከሆነ እኛም በኢትዮጵያ የምንገኝ ካህናት በተቻለንና ዓቅማችን በሚፈቅድልን መጠን ልማቶችን በማልማትና ገቢ የሚገኝበትን ዘዴ በማቋቋም ቤተ ክርስቲያናችን እንድትስፋፋ ምእመናን እንዲበዙና በሃይማኖት እንዲጎለምሱ ስብከተ ወንጌልም በመላ ኢትዮጵያ እንዲደረስና እንዲሰበክ መውጣት መውረድ ከባድ ጥረትም ማድረግ ግዴታ ይኖርብናል።

ይህ ካልሆነ ግን የሰውን እጅ ከመመ

ተከታዩ ወደ ገጽ ፲፪ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ጊዮርጊስ ሊቀ ሰማዕታት

የቅዱስ ጊዮርጊስ አባቱ ዘሮንቶስ እናቱ ቴዎብስታ የተባሉ ሲሆኑ የአባቱ ሀገር ቀጰዶቅያ የእናቱ ሀገር ልዳ ነው ። ዘሮንቶስ አባቱ በፈቃደ እግዚአብሔር ከቀጰዶቅያ ወደ ልዳ ሄዶ ተቀመጠ በዚያም ቴዎብስታ የምትባል ሴት አግብቶ ቅዱስ ጊዮርጊስን ወለደ ዘሮንቶስና ቴዎብስታም መልካም ክርስቲያኖችና ሀብታሞችም ነበሩ እግዚአብሔርንም ይወዱ ነበር በዚህም ደግነታቸው የተመረጠና የተቀደሰ ልጅ እግዚአብሔር ስለሰጣቸው ደስ ብሎአቸው ሲኖሩ የቅዱስ ጊዮርጊስ አባት የአውራጃ ገዢ ሁኖ ተሾመ ከዚህም መካከል የሮም ነገሥታት ኃላስና ኃራስይባሉ ነበር በብዙ ሀገሮች ላይ ኃይል አግኝተው ነገሥታቱን ሁሉ በበታቻቸው አድርገው ሁለቱ ነገሥታት ሲገዙ የፈጠራቸውን እግዚአብሔርን ትተው ጣዖት አቁመው ለጣዖት ይሰግዱ ጀመር ጊዮርጊስ በተወለደባት ሀገር ግን የክርስትና ሃይማኖት እንደተጠበቀ ነበር ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ወላጆች ልጃቸውን ጊዮርጊስን በንክብካቤና በጥንቃቄ አሳድገው ፯ ዓመት ሲሆነው ተማሪ ቤት አስገቡት በዚያም መንፈሳዊና ሥጋዊ ትምህርቱን ሲከታተል ጊዮርጊስ የ፲ ዓመት ልጅ እንደሆነ አባቱ ዘሮንቶስ ሞተና በምትኩ ሌላ ሀገረ ገዥ ተሾመ ጊዮርጊስንም ስለወደደው ያ አገረ ገዢ እናቱን አስፈቅዶ ከቤቱ ወስዶ እያስተማረ አሳደገው አዋቂና ንቁ መሆኑን ተመልክቶ መቶ ወታደሮችን ከሕይወት ታሪኩ ጋር ጨምሮ ንጉሡ ሹሞ መልሶ እንዲልክለት ላከው ንጉሡም የጊዮርጊስን አቋምና የሕይወት ታሪኩን ተመልክቶ በላከው ሀገረ ገዢ ውስጥ የአምስት ሺህ የወታደር አለቃ ሁኖ እንዲሠራ ሹሞ አባቱ ከወሰነለት ሀብት ሌላ አራት መቶ ወቄት ብር በየወሩ ደመወዝ እንዲያገኝ ጽፎ ሸልሞ በክብር ወደ ሀገሩ ላከው ።

ያሳደገው ሀገረ ገዥም በክብር ተቀብሎ የተሾመበትን ሥራ እንዲሠራ ለሕዝቡ አስተዋውቆ በሥራው መደበው የሀገረ ገዢም ከአንዲት ሴት ልጅ በስተቀር ሌላ ልጅ የለውም ነበርና ልጁ ሚስት እንድትሆነው አጭቶለት ሳለ



ቅዱስ ጊዮርጊስ ሊቀ ሰማዕታት

ሳይድረው በድንገት በጽኑ ሕማም ስለታመመ በቤቱ ያለ ንብረቱን ለጊዮርጊስ እንዲሰጡለትና ያጨለትን ሴት ልጅ እንዲድሩለት ተናዞ ሞተ በዚህ ጊዜ የጊዮርጊስ እድሜው ፳፩ ነበር ከዚህም መካከል የሮም ነገሥታት ኃራስና ኃላስ ከፋርሱ ንጉሥ ከዱድያኖስ ጋር ተጋጥመው ሲዋጉ የፋርሱ ንጉሥ ዱድያኖስ ስለአቸነፈ በኃይል የብዙ ሀገሮችን ነገሥታት አቸንፎ የ፸ ነገሥታት የበላይ ንጉሠ ነገሥት ሁኖ የግፍና የጭካኔ ሥራ ይሠራ ጀመር ክርስቶስን ክዶ እንደናቡከደነፆር የወርቅና የብር ምስል አጵሎስ የሚባል ጣዖት አቁሞ ይሰግድ ጀመር በነገሠባቸውም ሀገሮች ላይ አንድ ቀን እንኳን ጉብኝትና ፍርድ ሳይደርስ በፋርስ ከተማ ላይ የበታቾቹን ነገሥታት ሰብስቦ ተቀመጠ ። ቆራጡ ጀግና ቅዱስ ጊዮርጊስም በዚህ ግፈኛ ንጉሥ ዘመን መደሰት አልፈልግም ብሎ የታጨችለትን ሴት ልጅ ሳያገባ ድንግል ንጹሕ እንደሆነ ያለ የሌለውን ንብረቱንና ሀብቱን ለእናቱና ለእኅቶቹ እንዲሁም ለድሆች አከፋፍሎ ሰጥቶ አሽከሮቹን በነፃ አሰናብቶ ሁለት አሽከሮች ብቻ መርጦ ተከታዮቹ ቢሞት እንደሚቀብሩት ወስኖ አንድ ነጭ ፈረስ ከነ መሥሪያው አዘጋጅቶ የክርስቶስን አምላክነት የካደውንና የክርስትናን ሃይማኖት ጠላት የሕዝብን ጨቋኝ ገዢን ለመቋቋም ስለክርስቶስ መከራ ለመቀበልና የክርስቶስን አምላክነት ለመመስከር በመጀመሪያ በፈቃደ እግዚአብሔር ወደቤሩት ሀገር ሔደ ይህችም ቤሩት ከኢያሪኮ አዋሳኝ የምትገኝ ናት በዚችም ሀገር የሚኖር ሕዝብ ፈጣሪውን ክርስቶስን ክዶ ደራጐን የሚባል ዘንዶ አምላክ አድርጐ ሴት ሴት ልጁን ምግብ እንዲሆኑት እየገበረ ሲኖር በመጨረሻ የሀገረ ገዢው ልጅ ተራዋ ደርሶ ዘንዶው እንዲበላት ወደጫካው ወስደው አስቀምጠዋት ሳለ አጋጣሚ ሁኖ ቅዱስ ጊዮርጊስ በነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ሲያልፍ የቤሩት ሀገረ ገዢን ልጅ አገኛት ምን ሁነሽ ወደዚህ መጣሽ ቢላት የዚህ ሀገር ሕዝብ ሴት ሴት ልጃቸውን በፈረቃ ለአምላካቸው ለዘንዶ ምግብ እንዲሆነው ስለሚሰጡ የእኔም ተራየ ደርሶብኝ አምጥተው ጥለውኝ የዘንዶውን መምጣት እጠባበቃለሁ የዘንዶውም ስም ደራጐን ይባላል አለችው ያች ለዘንዶ የተዳረገች ሴት ልጅም

እንዳለችው ደራጐን የተባለው ሰይጣን ያደረበት ዘንዶ በእግሩ እያኮበኮበ በክንፉ እየበረረ በጭራው ጫካውን እያማታ ከመኖሪያ ቦታው ተነሥቶ የተዳረገችለትን ልጅ ለመብላት ሲመጣ ቅዱስ ጊዮርጊስን አይቶ ሊበላው ምላሱን አውለበለበ በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጊዮርጊስ በስመ አብወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብሎ በያዘው ትምእርተ መስቀል ቢአማትብበት ፈዞ ቆመ በዚህ ጊዜ ከፈረሱ ወርዶ በሰይፉ መታጠቂያ አንገቱን አሥሮ ያችን ከዘንዶ አፍ የዳነችውን ሴት ልጅ እያስጐተተ እስከ መካከለኛዋ የቤሩት ሀገር ደርሶ ለተሰበሰበው ለሀገሪቱ ሕዝብ የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ሆይ ይህ ደራጐን የተባለ ዘንዶ ሰይጣን ስለአደረበት ፈጣሪያችሁን አስክዶ ሴቶች ልጆቻችሁን እየተገበረ መጫወቻ ያደረጋቸው ጠላታችሁ ነው እንጂ አምላክ አይደለም አምላካችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሎ በፈረሱ ላይ ተቀምጦ በያዘው ትምእርተ መስቀል ጦር ወግቶ ከገደለው በኋላ ሕዝቡን አስተምሮ በማጥመቅና የክርስቶስን ሥጋና ደም በማቀበል ዘንዶው ደራጎን በሞተበትና በመካከለኛዋ ቤሩት ላይ ሁለት ቤተ ክርስቲያን ከአስተከለ በኋላ ከዚያ ተነሥቶ ወደፋርስ ሀገር ደርሶ ከንጉሡ ዱድያኖስ ቀርቦ ንጉሥ ሆይ የእግዚአብሔር መልክተኛ ክርስቲያን ነኝ ስሜ ጊዮርጊስ ይባላል ።

አሁን የመጣሁት ወንጌልን ላስተምር ነው እንጅ ሰው በሠራው ደካማ ጣዖት መስገድህና ማስገድህ ከንቱ ነው ሊሰገድለት የሚገባው ሰማይንና ምድርን ጠቅላላ በዓለሙ የሚገኘውን ለፈጣሪ ለእግዚአብሔር ብቻ ነው በነገሥክበት ሕዝብም ላይ የግፍና የ ጭካኔ ሥራህን አቁም ሕዝብህን እየተዘዋወርክ በመጐብኘት እውነተኛ ፍርድ ስጥ ሲል በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምንሃለሁ ብሎ ትምህርት ቢሰጠው ንጉሡ ዱድያኖስ ከተገዦቹ ነገሥታት ጋር ሁኖ የት ሀገር የመጣህ ደፋር ነህ ? ማንስ ላከህና ነው እንደዚህ ያለ ድፍረት የተናገርከው በል አሁንም እኔ ላቆምኩት አምላክ ስገድ ባትሰግድ ግን ከባድ ሥቃይና መከራ ይደርስብሃል እንዲሁም አሁን የተናገርከውን ነገር ደግመህ ብትናገር የሞት ቅጣት ይከተልሃል ለመሆኑ እግዚአብሔር የሚለው እንደምንያለ ኃይል ቢኖረው ነው እንደዚህ ያለ መልእክት

የሚልክህ እስኪ እርሱ መጥቶ ሲያድንህ አያለሁ ብሎ በቁጣ ቃል ለጣዖት እንዲሰግድ አስገደደው በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጊዮርጊስ ለዚህ ርኩስ ጣዖትህ አልሰግድም መናገሬንም የሚከላከለኝ የለም

ለምትገዛተውም ጉዳይ አምላኪየ ክርስቶስ ኃይሉን ጽንዓቱን ይሰጠኛል ። አልፈራም የፈለግከውን ማድረግ ትችላለህ ብሎ ሲናገር ለጊዜው በሥር ቤት ይደርና አስፈላጊው ጉዳይ ነገ ይፈጸምበት ብሎ ስለአዘዘ ወደ እሥር ቤት ተወስዶ አደረና በማግሥቱ በእንጨት እንዲሰቀል አዘዘ ከዚያም እንደኳስ ወደሰማይ እንዲወረወርና በድጋሚ በደረቅ ቆዳ እንዲታሠርና እንዲገረፍ አንጀትን በጣጥሶ የሚጥል መርዝ እንዲጠጣ የብረት ምስማር ጫማ አድርጐ እንዲሄድና ከሥጋው ጋር እንዲጣበቅ አካሉ ከሁለት ተሰንጥቆ በእሳት እንዲቃጠልና አመዱ በደብረ ይድረስ ተራራ ለነፋስ ተዘርቶ ድራሹ እንዳይገኝ ሥጋው ተፈጭቶ ለበሬ ምግብ እንዲሆን በመጋዝ እንዲተረተር በምሳር እንዲፈለጥ በምስማር ከግንድ ጋር እንዲቸነከር በመዶሻ እንዲቀጠቀጥ በጦር እንዲበሳ ሌላም ለሰው ጆሮ የሚቀፍ ለዓይን የሚያጸይፍ ሰውነትን የሚዘገንን ተቆጥሮ የማያልቅ ብዙ የብዙ ሥቃይ እንዲደርስበት አዞ በቅደም ተከተል ይህ ሁሉ ሥቃይ ተፈጸመበታል ።

እነዚህም ዓበይት ሥቃዮችና መከራ

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ከገጽ ፲፩ የዞረ

ልክት ነፃ የምትሆንበት ጊዜ አይኖርም ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን በጥገት ላም ልንመስላት እንችላለን ታዲያ ጥገት ላም ተገቢና አስፈላጊ የሆነውን ወተት ለመስጠት እንድትሰጥ የሚያስፈልጋትን መኖ እየሰጡ በእንክብካቤ እንደ ሚይዟት ሁሉ ቤተ ክርስቲያናችንንም ምንም እንኳን በጥገት ላም ብንመስላትም በበለጠ ከዕለት ወደ ዕለት እየተስፋፋች እንድትሄድ የሚያስፈልጋትንና የሚያስፋፋትን ልማት ማቋቋም ግድ ያስፈልጋታል እንላለን ።

ከነፈርግብ ማርቆስ





www.ethiopianorthodox.org

ዎች እየተፈጸሙበት እስከ ሰባት ዓመት ድረስ ቆየ ቅዱስ ጊዮርጊስ እነዚህን የመሰሉ አሰቃቂ መከራዎች ሲፈጸሙበት ባለመሰቀቅ በደስታና በትግሥት እስከ ሕይወት ፍጻሜው ድረስ በመቀበሉ ብዙ አስደናቂዎች የሆኑ ተአምራት አድርጐአል ብዙ ሰዎች አምነው የክርስቶስ ቤተሰቦች እንዲሆኑ አድርጓል የንጉሡን ሚስት እስክንድርያ ንግሥትን አሳምኖ ሰማዕት እንድትሆን አድርጓል ሦስት ጊዜ ሙቶ ፈጣሪው ከሞት አንሥቶታል አካሉ በእሳት ተቃጥሎ አመድ ከሆነ በኋላ ጥር ፲፰ ቀን በደብረ ይድራስ ተራራ በነፋስ ከተዘራና ከተበተነ በኋላ የተበተነው አመድ በእግዚአብሔር ተአምራታዊ ኃይል በየቅጠሉ ላይ ጊዮርጊስ ጊዮርጊስ እያለ ተገኝቷል ንጉሡን አስፈርቷል ከታሠረበት ቤት ብርሃን ሲበራ ታይቷል ።

የታሠረበት ግንድ በቅሎ ልምላሜ አሳድጓል መሬትን ረግጦ በተአምር ውሃ አፍልቆ ብዙ አማንያን እንዲጠመቁ አድርጓል ። ጃሮውና አፉ እግሩ የተሰነከለውን ስንኩል አድኖአል የሞተ ሰው አሥንሥቷል በተአምር በታሠረበት ቤት ምግብ እንዲገኝ አድርጐአል ከሰባት ዓመት በኋላ ከዚህ ዓለም በሚለይበት ዋዜማ ስሙን ጠርቶ በስሙ የሚማፀነውን በስሙ መከራ የሚቀበለውን ዝክሩን የሚዘክረውን በስሙ ቤተ ክርስቲያን የሚያንጸውን በስሙ ለድኃ የሚራራውን ሁሉ ፈጣሪው ክርስቶስ አሥራተ ምሕረት እንዲያደርግለት በጸሎት ተገናኝቶ አሥራት እንደተቀበለ ገድሉ ይናገራል ንጉሡ ዱድያኖስም በቅዱስ ጊዮርጊስ ያለውን ኃይል ካደነቀ በኋላ አማራጭ ዘዴ ፈልጎ አንገቱን በሰይፍ እንዲቆረጥ አዘዘ ቅዱስ ጊዮርጊስም ወደሚሞትበት ቦታ ወስደው እንዳቆሙት ወደፈጣሪው ክርስቶስ እንደዚህ ብሎ ልመና አቀረበ አቤቱ ክርስቶስ ሆይ ! እንደነቢዩ ኤልያስ ከዚህ ከሐዲ ንጉሥ ጋር የተሰበሰቡትን ነገሥታትና ንጉሡን ዱድያኖስን ጣዖቱን አጽሉስን እሳት ከሰማይ መጥታ እንድታቃጥላቸው እዘዝ ባለ ጊዜ እሳት ከሰማይ መጥታ ...ቃጥላቸዋለች ። ከዚያም አያይዞ ሰባት አክሊላተ ብርሃን ከፈጣሪው ክርስቶስ ተቀብሎ እንደፈጸመ ሲገሉት የታዘዙትን ባለወግዎች ፈቀደላቸው እነሱም እንደታዘዙ ሚያዝያ ፳፫ ቀን በዕለተ ዓርብ በ፱ ሰዓት አንገቱን በሰይፍ ቆርጠው ሲገድሉት ደምና ውሃ ወተት ከአንገቱ ፈሷል። ነፍሱን መላእክተ ብርሃን በክብር አሳርገዋታል ። ልዩ ልዩ ተአምራትም ተደርጓል ተከታዮቹም የቅዱስ ጊዮርጊስን አስከሬን ተሸክመው እንዘው ልዳ በሚባል ሀገሩ ቤተ ክርስቲያን ሠርተው ቅዳሴ ቤቱን ኅዳር ፯ ቀን አከበሩ የቅዱስ ጊዮርጊስንም አጽም በክብር ከቤተ መቅደሱ ውስጥ አግብተው አስቀምጠውታል እስከ ዛሬም ድረስ በመቃብሩ ብዙ ታምራት ሲሠራበት በዓለም ይገኛል ጊዮርጊስ በእግሩ በረገጣቸው ሀገሮች ሁሉ በስሙ ጸበል ፈልቆ ብዙ ልዩ ልዩ ተአምራት ይደረግበታል ።

ዛሬም እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ስሙን ጠርቶ በስሙ የሚማፀን ሁሉ ቅዱስ ጊዮርጊስ በረድኤት አይለየውም በዚህም ተራዳኢነቱ ፍጡነ ረድኤት ቅዱስ ጊዮርጊስ እየተባለ ይጠራል ። የቅዱስ ጊዮርጊስን ሥዕልና ስሙ የተጻፈበትን ይዞ ወደጦር ሜዳ ቢሔድ የጠላትን ኃይል የመደምሰስ ሥልጣን አለው የክርስትና እምነት ያላቸው ሰዎች የቅዱስ ጊዮርጊስን ታቦት ወደጦር ሜዳ ይዘው ቢዘምቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ በረድኤት አይለይም ።

ይህም በሀገራችን በአድዋው ዘመቻ እንደተገለጸው አባቶች ይመሰክራሉ ። ጠቅላላ የቅዱስ ጊዮርጊስ ተአምራታዊ ሥራው ብዙ ነው ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የዚህን ታላቅ ሰማዕት የቅድስና ሥራ ተመልክታ ገድል ጽፋ አጽሙ የተዘራበትን ጥር ፲፰ ቀን ያረፈበትን ሚያዝያ ፳፫ ቀን ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያኑን ኅዳር ፯ ቀን በከፍተኛ ሥነሥርዓት ታከብራለች ።

አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ



# ታቦተ ጽዮን ጽላተ ሙሴ

ስለ ታቦተ ጽዮን የሚነገር አጭር የሐተታ ቃል በግዕዝ ግሥ ተጸወነ ማለት ተጠጋ ማለት ነው።

ጸወን ማለት መጠጊያ ፣ ጽዮን ማላት ጥግ ማለት ነውና ። ለጊዜው ጽዮን የዳዊት ከተማ ደብረ ጽዮን ናት ፣ ፍጻሜው ግን የእመቤታችን ማርያም ምሳሌ ናትና ።

ስለዚህ ጽዮን ማለት 2ተኛው ትርጓሜ ታቦተ አምላክ ፣ ታቦተ ሥርዐት ወሕግ ፣ ምስማከ ሥጋ ወነፍስ ፣ ማኅደረ አምላክ ፣ ወማኅደረ መለኮት ፣ ማለት ነውና ፣ የድንግል ማርያም ምሳሌ የሆነችው ይህች ታቦተ ጽዮን በድንኳን ፭፻ ዘመን ኖራለችና ፣ ከዚያም በኋላ ንጉሡ ሰሎሞን የዳዊት ልጅ ቤተ መቅደስን በ፬ሺ፭፻ ዘመን ስለ ሠራ በቤተ መቅደስ ተቀምጣለች ።

ከዚያ በኋላ ጌታ ባወቀ በረቂቅ ምሥጢሩ ፣ የናቡከደናፆር ምርኮ (ፄዋዌ) ሳይደርስ ሰሎሞን የሠራው ቤተመቅደስ ሳይፈርስ ታቦተ ጽዮን አስቀድማ በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን በ፬ሺ፭፻፲፰ ዓ. - ዓ. ኢትዮጵያ መጥታለች ። ይኸውም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፱፻፹፪ ዓመት ቀድማ ነውና ።

ይኸንንም ከ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. ላይ ቢደምሩት ፪ሺ፱፻፶ኛ ዓመት በዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ በ፸፯ ዓ.ም. ሆነ ማለት ነውና ። ባለቤቱ ሕያው እግዚአብሔር እስራኤል ስለ በደሉትና ስላሳዘኑት ናቡከደናፆርን ለቅጣትና ለጥፋት ከፋርስ ፣ ዛሬ ኢራን ከተባለው አገር ወደ ኢየሩሳሌም ሳያመጣው ታቦተ ጽዮንን አስቀድሞ ወደ ኢትዮጵያ እንድትመጣ አድርጎ አክሱም ከተማ ላይ እንድትቀመጥ አደረገልን ። ይኸውና ዛሬም በትግራይ ከተማ አክሱም ላይ ተቀምጣ የእግዚአብሔር አምልኮና ምስጋና ሲነገርባትና ጌታ ሲሠለስና ሲቀደስባት ትኖራለች ።

ቀድሞም ታቦቷ በቅድስት አገር በኢየሩሳሌም ልዩ ልዩ ታምራት እያደረገችና እሥራኤልን እየተራዳች እንደኖረች በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳ. ከምዕ ፭-፯ ተመልከት ደግሞ ሳሙ ካልዕ ምዕ ፮ቁ. ከ፩-፳፫።ደግሞም በመቅድመ ተአምር ፣ አመ ፳ ወ ፩ ለኀ ወርኀ ጽዮን ተቅዋመ ማኅቶት ዘርእየ ዘካርያስ ፣ ይላል ። በዚህ ወር በ፳፩ ቀን ታቦተ ጽዮን ተማርካ በብሔረ ኢሎፍሊ ሔዳ ሳለች በላይ የነበረ፣በላይ የተቀመጠ ዳጎንን አውርዳ ጥላ ቀጥቅጣ አጥፍታ ለእስራኤል ተድላ ደስታውን ያሰማችበት ለሰብአ ኢሎፍሊ ኃይሏን ታምራቷን ያሳየች በትና የገለጠችበት ቀን ነው ።

ኋላም ዳዊት ነግሦ ልብሰ መንግሥቱን ለብሶ ዘውዱን ደፍቶ እመቤታችን ታቦተ ጽዮን ከቤተ አቢዳራ ስትመለስ በእልልታ በግርግርታ በይባቤ በቃለ ቀርን በዝማሬ የተቀበለበት ቀን ነው ። ደግሞ ዕዝራ ፣ ዘርእያ እንዲል ፣ ዕዝራ በአምሳለ ብእሲት ያያትን ዝካርያስ ወልደ ሐደ እያቶ በብርሃን ፋና ፣ በብርሃን መቅረዝ ተቅዋመ ወርቅን የመሰለበት ቀን ነው ። ፍልስጥኤም ማለት በዕብራይስጥ ነውኢሎፍሊ ማለት በዕርዕ ነውና ።

ያን ጊዜ እግዚአብሔር እሥራኤል ስለ በደሉትና ስለ ተቀየመ እስራኤልን በፍልስጥኤሞች እጅ ጣላቸው የኤሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ ፣ በደልና ግፋቸው ስለ በዛ በመጀመሪያው ጦርነት ፬ሺ ጀግኖች ከእስራኤል ወደቁ 2ተኛ ደግሞ ገጥመው ጦርነት አደረጉና ፣ እስራኤል ድል ሆነው ተመቱ ታላቅ ገድያ ሆነ ። ያን ጊዜ ከእስራኤል ወገን ፴ሺ እግረኞች ወደቁ ጌታም የመጣላቱ ምልክት ፣ ታቦቷ ተማረከች ፣ ፪ቱም የሊቀ ካህናቱ የኤሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ ፣ በጦርነቱ ላይ ሞቱ በጠቅላላው ከእስራኤል በጦርነቱ ላይ የሞቱት ፴፬ሺ ናቸው ።

እስተዋይ ልቡና ላለው ሰው እግዚአብሔር ሲቆጣ የማያዳላ እውነተኛ አምላክ ስለሆነ ታቦቱን ታቦት፡ቁሱን ቁስ መቅደሱን ቤተ ክርስቲያኑን ቤተ ክርስቲያን ጳጳሱን ጳጳስ መነኩሴውን መነኩሴ ፣ አይለውምና ኢየኃፍሮ ለባዕል እንበይነ ብዕሉ ወኢይምሕሮ ለነዳይ እንበይነ ንዴቱ ለእመ ኢኮነ መሥመሬ ሎቱ እንዳለ አትና በቅዳሴው ።

በእስራኤል በደልና በካህናቱ በአፍኒንና በፊንሐስ ኃጢአት የእግዚአብሔር ማደሪያ ታቦቲቱ ተማርካ በጠላት እጅ ገባች ፣ ፍልስጥኤሞችም ታቦቲቱን ወደ ከተማቸውወስደው ከጣዖቱከዳጎን ቤት አግብተው በዳጉን አጠገብ አስቀመጧት ፣ በበነጋው ጧት ማልደው ከዳጎን ቤት ሲገቡ ዳጐን በታቦቲቱ ፊት በምድር ላይ በግምባሩ ተደፍቶ ወድቆ ስለ ነበር ፣ አንሥተው ከሥፍራው መለሱት ፣፪ተኛም ደግሞ ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት እንደዚሁ ጧት ቢመጡ በግምባሩ ወድቆ አገኙት ፣ የዳጎንም እራሱና እጆቹ ተቆርጠው በመድረኩ ላይ ወድቆ አገኙት ደረቱ ብቻውን ቀርቶ ነበር ። ከዚህ በኋላ የዳጎን አገልጋዮች ካህናቱ ወደ ዳጎን ቤት መግባትን ፈሩ ተንቀጠቀጡ ምንም ጌታ ቢጣላ እንደ ተጣላ አይቀርም ይቅር ባይ ነውና በዕበጥና በልዩ ልዩ መቅሠፍት መታቸው ከዚህ በኋላ ይህች ታቦት በፍልስጥኤማውያን አገር ፯ ወር ተቀመጠች ።

ከዚያም ወስደው ወደ አሚናዳብ ቤት አገቧት አሚናዳብ ከሚባለው ሰው ቤት የእግዚአብሔር ታቦት ፳ ዓመት ያህል ተቀመጠች ። ከዚያም በላይ እንደ ገለጥነው ፳ ዓመት ከ፯ ወር ከሆናት በኋላ ዳዊት ደግሞ ከእስራኤል የተመረጡ ፫ሺ ያህል ሠራዊት ሰብስቦ ከአሚናዳም ቤት የእግዚአብሔርን ታቦት ለማምጣት ሄደና በአዲስ ሠረገላ አስቀምጦ ወደ (ኢየሩሳሌም) ደብረ ጽዮን ለመውሰድ ዳዊትና የእስራኤል ሠራዊት ሁሉ በዕብራይስጥ ቋንቋ በቅኔና በበገና በመሰንቆና በከበሮ በነጋሪትና በጸናጽል ድምፅ በእግዚአብሔር ፊት እያጨበጨቡና እየዘፈኑ ሲሄዱ ሠረገላ



www.ethiopianorthodox.org

ው የተጫኑባቸው ገደሮች መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እያደረጉ ሲፋንኑ አዛ የሚባለው የአሚናዳብ ልጅ እጁን ዘርግቶ የእግዚአብሔርን ታቦት ያዘ ስለ ድፍረቱ ወዲያውኑ ተቀሠፈ ። ያን ጊዜ ይኸን ስላየ ዳዊት አዘነ በጣም ደነገጠና ፈራ የእግዚአብሔር ታቦት እንዴት ወደ እኔ ይመጣል ብሎ ስለ ፈራ ዳዊትም ከዚህ በኋላ ታቦቷን አቢዳራ በሚባለው ሰው ቤት አግብቶ ፫ ወር ያህል ተቀመጠች። ጌታም የአቢዳራን ቤተሰቡንና ሀብቱን ባረከ ፤ የመከነው ወለደ ። ቤቱን ንብረቱን ሀብቱን ገንዘቡን ሁሉ አበዛለት ።

ዳዊትም የአቢዳራ ቤት መባረኩን ስለ ሰማ መንፈሳዊ ቅንዓት ስለ ቀናታቦቷን ወደ ደብረ ጽዮን ከተማ በደስታ አስመጣት ። ታቦቷን የተሸከሙ ካህናት ፮ እርምጃ በተራመዱ ቁጥር ዳዊት አንድ በሬና ፩ የሰባ ዳንገሌ አረደ ። ዳዊትም ከደስታው ብዛት የተነሣ በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በሙሉ ኃይሉ ይዘምር ነበር እስራኤል ሆ እያሉ (ቀንደ መለከት) እየነፉ ታቦቷን አምጥተው ከድንኳን አገቡ ያን ጊዜ ዳዊት እእምሮውን አጥቶ ሲዘፍን የሳኦል ልጅ ሚስቱ ሜልኮል በመስኮት ሆና ትመለከት ነበረችና ዳዊት ንጉሡ ሲዘፍን አይታ የተዋረደ መስሏት በልቧ ናቀችው ።

አባ ቸርነት ጋሻው በዛ

# መርቆሬዎስ ሰማዕት

ከዲዮቅልጥ ያኖስ ዘመነ መንግሥት ከ280 ዓ.ም አንሥቶ በተከታታይ የተነሱት የሮም ነገሥታት ከእግዚአብሔር ይልቅ ለጣዖትና ለምስል የሚሰግዱ አረማውያን ስለነበሩ ከዚህ አረማዊ ጠባያቸው የተነሣ በዘመናቸው የነበሩት ክርስቲያኖች በሰላም እንዲኖሩ ዕድል አልሰጧቸውም ።

ይልቁንም ፈጣሪያቸውን ክደው ጣዖት እንዲያመልኩና ለሰው ሰራሽ ምስል እንዲሰግዱ እያስገደዱ ያሰቃይዋቸው ጀመር ክርስቲያኖች ግን የስም ክርስቲያን ስላልሆኑና በነገሥታቱ ዘንድ ተወደው ምድራዊ ሀብትን ከማግኘት ይልቅ በሰዎች ዘንድ ተጠልተው በክርስቶስ ስም መከራን እየተቀበሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባትን የመረጡ እውነተኞች አማኞች በመሆናቸው ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን በመከራ ተፈትነው ድልን ለመቀዳጀት እስከበቁ ድረስ መንፈሳዊ ተጋድሏቸውን ቀጠሉ ።

ነገሥታቱም እልኩ ስለያዛቸውና ስይጣንም ስለሚገፋፋቸው በክርስቲያኖቹ ላይ ክንዳቸውን አንሥተው የተለያ ሥቃይ ቢያሳያቸውም መከራ መስቀሉን ሊሸከም የማይወድ ሊከተለኝ አይችልም የ ሚለውን አምላካዊ ቃል በማስታወስና መመሪያም በማድረግ አምላካችንን አንክድም በማለታቸው ምክንያት የሚደርስባቸውን መከራ ሁሉ ታግሰው ከራሳቸው ይልቅ ክርስቶስን እንደሚወዱ በገሐድ አስመስከሩ ከዚህም የተነሣ በሰይፍ ተከለሉ በእሳት ተቃጠሉ ለአራዊት ተጣሉ ። ልዩ ልዩ ፀዋትወ መከራንም ሁሉ ተቀበሉ ።

ስለክርስቶስ ሲመሰክሩና ስለእውነተኛ ሕይወት ሲያስተምሩ ራሳቸውን የሠውት መስተጋድላንሰማዕታትየሚባሉ ሲሆኑ ይህ አሰቃቂ ድርጊት የተፈጸመበት ዘመንም ዘመነ ሰማዕታት ተብሏል ። ከነዚህ ሰማዕታት መካከል ጥቂቶቹ ጽላት ተቀርጾላቸው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስማቸው ሲታወስ ይኖራል።ኅዳር 25 ቀን በየዓመቱ በዓሉ የሚከበርለት ሰማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዎስም በተጋድሏቸው በጣም ከታወቁት ከነዚህ ሰማዕታት አንደኛው ነው ።

የመርቆሬዎስ አባት ኖኅ የሚባል ሲሆን እናቱም ታቦት ትባል እንደ ነበር በመጽሐፈ ስንክሳር ተጽፏል ። የመርቆሬዎስ የመጀመሪያ ሰው ፒሉፖዴር ስመ ጥምቀቱ ግን መርቆሬዎስ ነው ። መርቆሬዎስ ማለትም የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ማለት ስለሆነ ይህንኑ ቋሚ የመጠሪያ ስም አድርጎ ተጠርቶበታል ።

ቅዱስ መርቆሬዎስ ለአካለ መጠን ሲደርስ ዳኬዎስ ለተባለ ንጉሥ በወታደርነት ተቀጥሮ ከንጉሡ ጋር ወደ ጦርነት ሄደ ። ንጉሡና ሠራዊቱ ጠላቶቻቸውን ድል አድርገው እንደተመለሱ ንጉሡ ለሠራዊቱ ግብዣ በሚያደርግበት ጊዜ በመጀመሪያ ለጣዖት ሠውቶ ሰግዶ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሲመለስ ቅዱስ መርቆሬዎስ ስላየ ሰው ድል ለሰጠው ለእግዚአብሔር በመስገድና እሱንም በማመስገን ፈንታ እንዴት ለሰው ሠራሽ ጣዖት ይሰግዳል ?“ በማለት ቅር ስላለውና አረማዊነቱንም በግልጥ ስላወቀ በዚሁ ተቀይሞ ወደ ግብዣው ሳይሄድ ቀረ ። በዚህ ጊዜ አድርባዮች ምክንያት ስላገኙ ወደ ንጉሡ ሄደው “ንጉሥ ሆይ መርቆሬዎስ የተባለው ባለሟል ወታደርህ ከግብር ! አልመጣም። ለምታመልከውም ጣዖት አልሰገደምና ይህ አንተን መናቅ ነው እንዲያውም አገዛዛሚያውን ስናየው የሚከዳህ ይመስላልና ይታሰብበት”ሲሉ አሳጡት ።

ንጉሥ ዳኪዎስ ይህንን እንደሰማ መርቆሬዎስን አስጠርቶ “ምነዋ ትወደኝ የነበረ ጠላኸኝ ?ላቆምኩት ምስልና ጣዖት ለምን አልሰገድክም ለምንስ መሥዋዕት አልሰዋህም” በማለት ቢጠይቀው ስለአንተም አገዛለሁ እኔ ግን ለጣዖት አልሰግድም “እግዚአብሔርንም አልክድም” በማለት በድፍረት መለሰለት ሙሉ ትጥቁንም አውልቆ ከንጉሡ ፊት ወረወረለት ።

ዳኬዎስ የመርቆሬዎስን ድፍረትና የሃይማኖቱንም ጽናት ባየ ጊዜ እጅግ ተበሳጨና እንዲገርፉት አዘዘ ከዚህም የተነሣ ከመጠን በላይ እየገረፉ እጅግ በጣም አሰቃዩት በኋላም የሮም ተወላጅ በመሆኑ የመርቆሬዎስን ግፍ ያዩ ሮማውያን ይነሣሡብን ይሆናል ። ብለው ሕዝቡን በመፍራት ንጉሡና መኳንንቱ ተማክረው መርቆሬዎስ እንደታሠረ ከሮም ወደ ቂሣርያ ልከውት በዚያ መከራና ሥቃይን እየተቀበለና ስለ ክርስቶስ እየመሠከረ ሣለ አንገቱን በሰይፍ ተከልሎ በሰማዕትነት አርፏል።

ሰማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዎስ ንጉሡ ዳኬዎስንና የእሱ መልእክተኞች የሆኑ አረማውያን በእሱ ላይ የፈጸሙትን ግፍና መከራ እስከመጨረሻው የሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ ታግሦ እግዚአብሔርን ሳይክድ ለጣዖትም ሳይሰግድ ይልቁንም የክርስቶስን ስም እየመሰከረ ለብዙዎች ክርስቲያኖች አብነት ሆኖ ተጋድሎውን ፈጽሞ በመሞቱ ሰማዕት ተብሎ መታሰቢያው ወር በገባ በ25 ጽላቱ ባለበት ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ሲታሰብ የሚኖር ሲሆን ይልቁንም ሕዳር 25 ቀን በየዓመቱ እንደዚሁ በዓሉ ይከበራል ።

ሕዳር ፳፭ ቀን የሚነበበው ስንክሣር እንደሚገልጠው ቅዱስ መርቆሬዎስ ከሞተ በኋላም ታላቅ ተአምራትን እንደ ፈጸመ ይተረካል ፤ ይኸውም ከዳኬዎስ ቀጥሎ የነገሠው ሌላው አረማዊ ንጉሥ ዩልያኖስ እንደዚሁ ለጣዖት ሰገዱ ፈጣሪያችሁን ካዱ እያለ ክርስቲያኖችን የሚያሠቃይና የሚያስጨንቅ በመሆኑ በእሱ ዘመነ መንግሥትም ብዙ ክርስቲያኖች በግፍ ተጨፍጭፈዋል ። እጅግም ተሰቃይተዋል ።

ስንክሣሩ እንደሚናገረው በዚሁ ዘመን የነበሩ ባስልዮስና ጎርጎርዮስ የተባሉ ሁለት ወንድማማቾች በሃይማኖት የተነሣ ከዩልያኖስ ጋር ተጣልተው በእሥር ላይ እያሉ ንጉሡ ጠላት ተነሥቶበት ወደዘመቻ ሲሄድ ሲመለስ እንደሚገድላቸው በቀጠሮ ላይ እያሉ ፋርስ በተባለው ሀገር ጦርነት ገጥሞ በመዋጋት ላይ እያለ እግዚአብሔር ቅዱስ መርቆሬዎስን በአካለ ነፍስ አምጥቶ በጦር ወግቶ እንዲገድለው አድርጓል ። በዚህም ጊዜ ከእስረኞቹ አጠገብ በቅዱስ መርቆሬዎስ ስም የተሠራ ቤተ ክርስቲያን ነበርና በዚያ ተሰቅሎ የነበረ የመርቆሬዎስ ሥዕል ከፈረሱ ላይ እንዳለ በደም ታልሎ ሲንጠባጠብ ባስልዮስና ጎርጎርዮስ በተአምራት አይተው ቀተልኮኑ ለዩልያኖስ ቢሉት ሥዕሉ በተአምራት አፍ አውጥቶ አወን ገደልኩት ብሏቸዋል ። ሕዳር ፳፭ ቀን እነዚህ ታሪኮች የተፈጸሙበት ዕለት በመሆኑ የቅዱስ መርቆሬዎስ ጽላት ባለባቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ገድሉ እየተነበበና ተአምራቱ እየተነገረ በዓሉ በታላቅ ክብር ሲከበር ኖሯል ወደፊትም ይቀጥላል ።

የሰማዕታትን ገድልና ተአምር የምንጽፈውና የምንናገረው ለከንቱ ሳይሆን እግዚአብሔርን እንዴት ማገልገል እንደቻሉና እግዚአብሔርም ምን ያህል በተአምራት ይጉበኛቸው እንደነበረ ለመግለጽና ምሳሌነቱንም እንድንከተል ነውና እያንዳንዳችን ክርስቲያኖች ለጣዖት ከመስገድና ባዕድ አምልኮንም ከመከተል ተከልክለን እግዚአብሔርን በእምነት እንከተከው ።

ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

# ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ቁር ሰው ነጭ ከነጭ ሰው ጥቁር መወለድ እንደሚችል የሚያስረዳ በዚሁ መጽሐፍ ተጽፏል ቃሉም ወውእቱ ላህም ሀዓዳ ዘኮነ ብእሴ ወጽአ እምገዘኩ መስቀር” ይላል ነጭ ላም የተባለው ሰው ኖኅ ሲሆን መስቀር የተባለውም የኖኅ መርከብ ነው ቀጥሎም ወሰለስቱ አልህምት ምስሌሁ ይላል ሦስት ላሞች የተባሉት የኖኅ ልጆች ሴም ካም ያፌት አብረውት እንደነበሩ ሲያመለክት ነው ስለመልካቸውም ሲገልጽ ፤

“ አኃዱ እምኔሆሙ ቀይሕ ከመ ደም ወአሐዱ ጸሊም ወውእቱ ገዘኩ ላህም ሀአዳ ኃለፉ እምኔሆም” ከ፫ቱ ላሞች አንዱ ነጭ አንዱ ቀይ አንዱ ጥቁር ነው በማለት ዘርዝሮ የጻፋቸው የነጩን የኖኅን ልጆች ሤምን ነጭ ፤ ካምን ጥቁር ፤ ያፌትን ቀይ ብሎ ለመናገር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ።

ይህንን በሰፊው ለመረዳት ቢያስፈልግ መጽሐፈ ሄኖክ መመልከት ነው ።

የእግዚአብሔር ልጆችና የሰው ልጆች የተባሉ እነማን ናቸው ? ለሚለው ጥያቄ ደግሞ የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉ ሕጉን ጠብቀው ትዛዙን አክብረው የሚኖሩ የሴት ልጆች ሲሆኑ የሰው ልጆች የተባሉት ደግሞ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ወጥተው በራሳቸው ፈቃድ ይኖሩ የነበሩ የቃኤል ልጆች ናቸው ።

ቀጥሎም ያለው ጥያቄ ሰው ከጥፋት የማይመለስ መሆኑን እያወቀ እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በመፍጠሩ ለምን ተፀፀተ የሚል ነው ።

እግዚአብሔር ሰውን ከአራቱ ባሕርያት ሲፈጥረው ክፉውንና ደጉን ለይቶ የሚያውቅበት አእምሮንም ጨምሮ ሰጥቶታል በተሰጠው አእምሮ የፈለገውን እንዲሠራም ነፃነት ተሰጥቶት ነበር በመጀመሪያ ከፍጥረታት በላይ አድርጎ የፈጠረውም ትእዛዙን ጠብቆ እንዲኖር ነበር የሰው ልጅ ግን በተሰጠው አእምሮ ሳይጠቀም በሰይጣን ቃል ተታሎ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በማፍረሱ ፈጣሪውን ሊያሳዝን ችሏል እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሚጠቀምበትን ሥልጣን ጨምሮ ፈጥሯል በተሰጠው ሥልጣን ሳይጠቀምበት ቢቀር ግን ራሱን ይጐዳል ፈጣሪውንም ያ ሳ





www.ethiopianorthodox.org

ዝናል ቅንጉት ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም እንደሚባለው ሰው ወደፊት ይሳሳታል ብሎ እግዚአብሔር አምላክሰውን መፍጠሩን አልተወውም ።

በመቅድመ ወንጌል "የወደደችውን ትሠራ ዘንድ ለነፍስ ሥልጣንን ሰጣት በምታደርገውም ተግባር ሁሉ የሚያሸንፋት አይኖርም" ተብሎ ተጽፏል ስለዚህ ሰው የሚበድል መሆኑን እያወቀ ለምን ፈጠረው ማለት ተገቢ ስላይደለ ማንኛውም ሰው በመልካም ሥራው ጠላቱን ሰይጣንን ድል ነሥቶ ከፈጣሪው የሚሰጠውን ክብር በተስፋ መጠበቅ ይኖርበታል ።

የመጨረሻው ጥያቄ እግዚአብሔር አምላክ በደለኞችን ሰዎች ከገጸ ምድር ሲያጠፋ ያልበደሉትን እንስሳት ጨምሮ ለምን አጠፋቸው የሚል ነው እንስሳት የተፈጠሩትየሰውን ልጅእንዲያገለግሉ ነው ይኸውም በመጀመሪያ አዳም ከፈጣሪው ጋር ሳይጣላ ገና በምድረ ገነት ሳለ እንስሳት አራዊት ወደ እርሱ እየመጡ አርደህ ብላን አልበህ ጠጣን በማለታቸው ይታወቃል ዘፍ. ፩-፳

ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክም ሰዎች ሲበደሉ የሚያጠፋው እነርሱ የሚጠቀሙባቸውን ጭምር ነው ። አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም የሰዎችን መጠቀሚያ እንስሳትን አጥፍቶ ሰዎችን የሚታገሥበት ጊዜ አለ ። በሌላበኩልደግሞ ለኃጥአን የወረደ ለጻድቃን እንደሚባለው ሰዎች ሲጠፉ እንስሳትም እንደሚጠፉ ያደርጋል ።

አባ ጊዮርጊስ አልቦ ዘይትዋስአዘንተ አህሠምከ ወዘንተ አሠነይከእግዚአብሔርን ይህንን አጥፍተሃል ይህንን አሳምረሃል" ብሎ የሚከራከረው የሚወቅሠውና የሚከሰው የለም እንደወደደ ያደርጋል እንደ አሰበም ይፈጽማል ብሎ እንደተናገረው እኛም ብንሆን ሥራህ እጅግ አስደናቂና አስገራሚ ነው እያልን እርሱን ከማድነቅ በስተቀር ሌላ መልስ የለንም ።

# የመንፈስ ቅዱስ ልዩ ልዩ ሀብታት

የሰው ልጅ ግዙፋዊ ነገሮችን የሚያጠናው የሚመረምረው በግዙፋዊ መሣሪያዎች ነው ። ከዚህ ውጭ ፣ ከግዙፋዊ ክሥተት ባሻገር ያለውን እውነታ መመርመርና ማወቅ ለምድራዊ ሰውእስከ አሁን አልተሰጠውም ። ይሁን እንጂ በሃይማኖት ሰዎች ይልቁንም በክርስትና ይህ ከመታወቅ በላይ የሆነ ምሥጢራዊ ዓለም ትርጉም ሳያገኝ አልቀረም። ምንም እንኳ ሰው ሥጋዊ ቢሆንም ከሌሎች ፍጥረት ሁሉ ተለይቶ በእግዚአብሔር አምሳያ የተፈጠረ፡የሕይወትእስትንፋስ ያለው መንፈሳዊ ደግም ነው ። መንፈስ ማለት የማይጨበጥና የማይዳሰስ ፣ የማይታይም ረቂቅ ነገር ነው ስለዚህ ሰው የግዙፉን ዓለም በምድራዊ መሣሪያና በሥጋዊ ዕውቀት ሲመረምር የረቂቁን ዓለም (መንፈሳዊውን) ደግሞ ያው በመንፈስ ይመረምራል ።እነዚህ ሁለቱ የራሳቸው የሆነ ልዩ ባሕርይ አላቸውና አንዱን በሌላው መሣሪያ ለማወቅ መሞከር ከቶውንም ወደ ዕውቀት አያደርስም። መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም ፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም ። መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል ራሱን ግን በማንም አይመረመርም (፩ ቆሮ.፪፣ ፲፣፲፬፣፲፭) ስለሆነም የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ግዙፉን ዓለም ከረቂቁ ፡ ሥጋዊውን ከመንፈሳዊው ለማወዳደር ሳይሆን የመንፈስን ነገር ለይቶ ለማመልከት ነው ።

እንግዲህ መንፈስ የምንለው የማይዳሰስና የማይታይ ረቂቅ ቢሆንም ስለ እርሱ ሊነገር የሚገባውና ሊታወቅ የሚችለው ብዙ መንፈሳዊ ነገር መኖሩን በቅድሚያ መገንዘብ ያሻል ። ሀብታቱንም ከመግለጽ በፊት ስለ መንፈስ ቅዱስ በጥቂቱ መናገር አስፈላጊ ይመስለኛል መንፈስ የሚለው ቃል ብቻውን ሲነገር ስለማንና ስለምን እንደተነገረ ትርጉሙ አሻሚ ሊሆን ይችላል ። ምክንያቱም የተለያዩ መናፍስት አሉና ። ስለሆነም የእግዚአብሔር መንፈስ የመላእክት መንፈስ የሰው መንፈስ ርኩስ መንፈስ (የጋኔን መንፈስ) እየተባለ ተለይቶ ይነገራል። ቢሆንም አሁን የተነሣሁበት ዋና ዓላማ ስለተለያዩ መናፍስት ለመተረክ አይደለም። ዳሩ ግን በርእሱ እንደተገለጠው ስለአንዱ የእግዚአብሔር መንፈስና ስለ ልዩ ልዩ ሀብታቱ በመጠኑ ለመናገር ነው ።

የእግዚአብሔር መንፈስ (መንፈስ ቅዱስ) ከሥላሴ አካላት አንዱ የሆነ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው (ማቴ ፳፰፣ ፲፱፣ ፪ ቆሮ ፲፫፣፲፬) ። ይህም ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደምንረዳው ከአብና ከወልድ ጋር ከዘላለም የነበረ ፣ በመለኮታዊ ክብሩ ከአብና ከወልድ ጋር የሚተካከል የባህርይ ሕይወታቸው አካላዊ መንፈስ ነው። ከሌሎች መናፍስት ለመለየትና የባህርይ ቅድስናውን ለመግለጥ "ቅዱስ" የሚል ቃል ተቀጥሎለታል። ቅድስናው የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባሕርይ እጅግ ግሩምነት፡ ሁሉን ቻይነትና ከመወሰን ነፃ የሆነ ፍጹምነት የሚገልጽ ነው። (ዕን ፩፡፲፫)። ቅድስናው የእግዚአብሔርነቱ ሁለንተናዊ ብርሃንነት ነው ፤ እንደ ፀሐይ ጨረር ቀለማትን አዋሕዶ ብርሃንን ይሰጣልና ። እግዚአብሔር ሁለንተናው የቅድስና ምንጭ ነውና ለፍጥረቱም ከቅድስናው አካፍሏል ። ለእያንዳንዱም ሰው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ታድሏል ። በመሆኑም ይህ ስም ለእግዚአብሔር መንፈስ ከሁሉም በላይየከበረየተጸውዖ ስምሆኖ አል።ይሁንእንጂ መንፈስቅዱስበመጽሐፍቅዱስ ውስጥ በእያሌ ስሞች ተጠርቶአል ። ይኸውም የእግዚአብሔር መንፈስ ፣ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ ፡ መንፈስ ፡ የጌታ መንፈስ ፡ የክርስቶስ መንፈስ ፡ የእውነት መንፈስ ፡ አጽናኝ (ጰራቅሊጦስ) ተብሏል ። እነዚህ ሁሉ የአንዱ መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ ስሞች ናቸው። እንዲሁም እስትንፋስ ፡ ነፋስ ፡ ርግብ ፡ የእግዚአብሔር ጣትና እሳት የሚሉ ምሳሌዎች ተሰጥተውታል ። በዕብራይስጥ ሩዋኅ ሲባል ፡ በግሪክ ደግሞ ፕኑማ ተብሏል ።



መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር ከዘላለም የነበረ ፡ ያለና የሚኖር በመሆኑ ሥራው በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ዘመን ታውቋል ። በሁለቱ ዘመናት ሥራው ልዩ አይደለምና መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይና በአዲስ ኪዳን ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚያስተምረን ተመሳሳይ ነው። የሚሠራው ያው አንዱ መንፈስ ቅዱስ ነው ። በእርግጥ የመንፈስ ቅዱስን ጉልህ ተግባር ሥዕላዊ መግለጫ ለማግኘት ወደ አዲስ ኪዳን ነባራዊ ክሥተት ዘወር ማለት ይኖርብን ይሆናል ። ዳሩ ግን ይህ የጌታችንና የሐዋርያት የተሟላ ትምህርት ከብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች ከምንማረው በምንም መንገድ አይጋጭም፡

"እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡..." (ዮሐ. ፬፡ ፳፬) ስለተባለ ፡ በአንዳንዶች አመለካከት የሥላሴ ሁለንተና በመንፈስ ቅዱስነት ብቻ ይታሰባል ። ይህ አሳብ የአብን ፡ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን ፍጹም አካላዊ ልዩነት ወደ ማፍረስ ይቃጣልና የተሳሳተ አመለካከት ነው። ሌሎች ደግሞ ስለመንፈስ ቅዱስ ሲናገሩ ፡ በአብና በወልድ መካከል የፍቅር ግንኙነት አድርገው ይገልጹታል ። በተጨማሪም "የእግዚአብሔር ሕያው ሥራ በዓለም ውስጥ" ብለው ይተረጉሙታል ። ይህም በከፊል እውነትነት ቢኖረውም ፡ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ መንፈስነት ወደ መካድና እርሱነቱን ዝቅ አድርጎ አንድ ዓይነት ግፊት ወይም ኃይል ወደ ማለት ስሕተት ያዘነበለ አተረጓጎም ነው ። መንፈስ ቅዱስ ግን የሚናገር ፡ የሚያጽናና ፡ የሚያስተምር፡ የሚወቅስ ፡ የሚመራና የጸጋ ሀብታትን የሚያድል አካላዊ መንፈስ ነው እንጂ ዝርው መንፈስ አይደለም ። (ዮሐ. ፲፬ ፡ ፲፮፡ ፳፮ ፡ ፩ ፡ ፮ ፡ ፳.፲፫ ፡ ፩ ቆሮ. ፮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ፡ ፬.፲፩) ። በመሆኑም መንፈስ ቅዱስ የአማኙን ልብ የሚያጠራና የሚለውጥ ፡ ስለ ኃጢአትም ዓለምን የሚወቅስ የእውነት መንፈስ ነው ። መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ ይኖራል ። በድካማቸውም ያግዛቸዋል ። (ሮሜ. ፰ ፡ ፳፮) ።

እዚህ ላይ በመንፈስ ቅዱስ ስለምን ታደለው የጸጋ ሀብታት ከመናገሬ በፊት "ጸጋ" "ሀብት" ስለተባሉት ቃላት ለመግለጽ እፈልጋለሁ ። ሀብት "ወሀበ"-ሰጠ ከሚለው የግእዝ ግሥ የወጣ ነው፡ ስለዚህ ሀብት ማለት ስጦታ ማለት ሲሆን ሀብታት በብዙ ነውና ስጦታዎች ማለት ነው። አንዳንዱ ሀብት ሲባል ገንዘብ ንብረት እንደሆነ ይተረጉማል ። ነገር ግን ቃሉ ከአማርኛ ስለተወረሰ እንጂ መሠረታዊ ትርጉሙ አይደለም ። "ጸጋ" የሚለውን ቃል ደግሞ ብዙዎች ስጦታ ብለው ይተረጉሙታል ። በእርግጥ ቃሉ "ጸገወ"-ሰጠ ከሚለው ግሥ የወጣ ስለሆነ "ጸጋ" ስጦታ መባሉ ስሕተት አይሆንም ።ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ የቃሉን አገባብ ከተመለከትን ይህ በቀሙ የተወሰደ ጠባብ አተረጓጎም ነውና የቃሉን ሙሉ ስሜት አይገልጽም ። ስለዚህ ጸጋ ተብሎ የተተረጐመው ቃል ሰፊ ሀሳብ ያዘለ በመሆኑ ፣ ስጦታ ብለን ብንፈታው ይዘቱን በጣም ያጠበዋል ። መጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈባቸው የዕብራይስጥና የግሪክ ቋንቋዎች የቃሉን ትርጉም በመመልከት የተሻለ ሀሳብ ማግኘት ይቻላል ። ጸጋ በዕብራይስጥ ሄን ሲሆን ፣ ግሪኩ ካሪስ ይለዋል ። ትርጉሙም ዋጋ ሊከፈልለት የማይችል ፡ ወሮታም የማይመለስለት የእግዚአብሔር በጎነት ለሰው ልጅ ሲሆን ፣ በውስጡ የእግዚአብሔር ፍቅር ፡ ይቅርታ ቸር ስጦታ ደግነት ፡ ንስሐና ተሐድሶ የተሰኙትን ሀሳቦች ይይዛል ። በተጨማሪም ጸጋ የእግዚአብሔርን ምሕረት ደግነት የመውደድ ቸርነትና መልካምነት የሚገልጽ ነው ። (ቲቶ ፫.፫፣፬-፯) ።

እንግዲህ ምእመናን የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ናቸውና (፩ ቆሮ. ፫፣፲፮ ፮፣፲፱) መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ልብ ሲኖር ፣ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ሀብታትን (ስጦታዎችን) እንደ በጎ ፈቃዱ ለእያንዳንዱ ያድላል ። ስጦታዎቹም የጸጋ ስጦታዎች ናቸው ። ስለእነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በተከታዩ ጽሑፌ ለማቅረብ እሞክራለሁ ።

ይቀጥላል

ተስፋዬ ረጋሣ



www.ethiopianorthodox.org

# የወት/ ሳባ ታደሰና የአቶ ሚ. ባባክር ድራሜ ጋብቻ በጸሎተ ተክሊል ተፈጸመ

የእነዚህ ወጣቶች ጋብቻ የተፈጸመው መስከረም 27 ቀን 1977 ዓ/ም አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ነው ።

በዚሁ ዕለት ከንጋቱ ፲፪ ሰዓት ከ፲፭ ደቂቃ ሲሆን ሙሽሮቹ በሚዜዎቻቸው ግራ ቀኝ ታጅበው ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን እንደደረሱ ሁለት ሕፃናት እቅፍ አበባ አበርክተውላቸዋል ። ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ገብተው ተሳልመው አጭር ጸሎት አድርገው በተዘጋጀላቸው መንበር እንደተቀመጡ ጸሎተ ተክሊሉ በብፁዕ አቡነ ገሪማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሱዳን ሊቀ ጳጳስና የልማትና ክርስቲያናዊ ተራይድኦ መምሪያ ተ/ዋና ጸሐፊ መሪነት ተጀምሮ እንደተፈጸመ ጸሎተ ቅዳሴው ቀጥሏል ።

ጸሎተ ቅዳሴውም የተመራው በብፁዕ አቡነ አብርሃም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል የበላይ ተጠሪ ነበር ። ብፁዕነታቸውም በጸሎተ ቅዳሴው ከዮሐንስ ወንጌል ፫.፳፯-፴፮ የሚገኘውን ኃይለ ቃል አንብበው መንፈሳዊ መልእክትን አስተላልፈዋል ። ባስተላለፉትም መልእክት ‘‘ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር ንትፈሣሕ ወንትሐሠይ ባቲ’’ የዛሬዪቱ ዕለት እግዚአብሔር ለእኛ ለወገኖቹ ታላቅ ሥራ የሠራባት ዕለት ስለሆነች እጅግ በጣም ልንደሰትባት ይገባናል ። ይህንንም ቃል የጠቀስኩት በዛሬዪቱ ዕለት የሴኔጋሉ ተወላጅ የሆነው ሚስተር ሚካኤል የቤተ ክርስቲያናችን አባል ፣ ከክርስቶስም ጋር አንድ አካል በመሆኑ ነው ብለዋል

ብፁዕ አቡነ አብርሃም ትምህርታቸውን በመቀጠል እረኛ ካልጠፋት ብዙ በጎች ጠፍቶ በተገኘው በአንዱ በግ ደስ እንደሚለው እኛም በዛሬዪቱ ዕለት የእኛ ቤተ ክርስቲያን አባል በሆነው ሙሽራ ከሌላው ጊዜ የበለጠ ደስታ ሊሰማን ይገባል ካሉ በኋላ ብፁዕነታቸው ትምህርታቸውን በማራዘም በጐንደር ዘመነ መንግሥት በጐንደር ከተማ ደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን መለኮቱን በገለጸበት ዕለት ነሐሴ ፲፫ ቀን ዓፄ ዳዊት ተገኝተው ነበር ።

በዚህ ጊዜ አንድ ሊቅ በቅኔ ለፈጣሪውና ለንጉሡ ዓፄ ዳዊት ምስጋና ሊያቀርብ ፈልጐ ‘‘ዮም ዕለተ ብዙኅ ትፍሥሕት እስመ በደብረ ታቦር ቆመ ፈጣሪ ወበደብረ ብርሃን ዳዊት’’ ሲል ተቀኝተዋል ። ወደ አማርኛ ሲተረጐም የዛሬው ዕለት ታላቅ የደስታ ዕለት ነው ፈጣሪ በደብረ ታቦር ሲቆም ዳዊት በደብረ ብርሃን ቆሟልና ማለት ነው።ስለዚህ እኛም በዚህ ሰዓት ይህንን ታላቅ ሥራ ላሠራ ፈጣሪ እንዲሁም እኛ በማናውቀው እግዚአብሔር በሚያውቀው መንገድ ስባ ወደ ክርስቶስ ላቀረበችው ሙሽሪት ምስጋና ልናቀርብ ይገባናል። በማለት ብፁዕነታቸው ትምህርታቸውን አጠቃለዋል ።

ጸሎተ ቅዳሴው በ፫ ሰዓት ከ፲፭ ደቂቃ እንደተፈጸመ በቤተ ክርስቲያኑ የነበረው ሕዝበ ክርስቲያን ሙሽሮቹን በልልታና በጭብጨባ ሸኝቷቸዋል ። ሙሽሮቹም ከሚዜዎቻቸውና ጥሪ ከተደረገላቸው ሰዎች ጋር ሆነው ቁርሱ ወደ ተዘጋጀበት ሒልተን ሆቴል አምርተዋል ፣ ከዚያም ሲደርሱ የሀገር ባህል ተጫዋቾች ‘‘ሙሽራዬ የወይን አበባዬ’’ እያሉ በሚያስደስት ሁኔታ ተቀብለዋቸዋል ። በዚያም የቁርሱ ግብዣ ቀጠለና በመጨረሻ ብፁዕ አቡነ ገሪማ ‘‘ሙሽሪት ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው’’ በሚል ርእስ ተንተርሰው ሰፋ ያለ ትምህርት ሰጥተዋል ። ብፁዕነታቸው በሰጡት ትምህርት በቅዱስ መጽሐፍ ክርስቶስ በሙሽራ ቤተ ክርስቲያን በሙሽሪት ተመስለው መነገራቸውን ጠቅሰው ዛሬ ሁላችንም በዚህ አዳራሽ የሰበሰን ሁለቱን ወጣቶች አንድ ያደረገው ቅዱስ ጋብቻ ነው ። ጋብቻን የሚከለክል ችግር ካልገጠመና በድንግልና ፣ በሕገ ምንኩስና ተወስኜ እግዚአብሔርን አገለግላለሁ ብሎ ወዶ በፈቃዱ በድንግልና ለመኖር ካልቆረጠ ሰው በስተቀር ሁሉም ሰው ረዳት እየፈለገ በማግባት እየተረዳዳ ቢኖር የሚከለከለው ነገር የለም ። ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት ። ብሎ እግዚአብሔር አምላክ ተናግሯልና ዘፍ. ፪.፲፰ ካሉ በኋላ ጋብቻ በተለያዩ መንገዶች ይፈጸማል ጥሩ ኅብረተሰብእ ሊገኝ የሚችለውም እንደዚህ በምሥጢረ ተክሊል የተፈጸመው ጋብቻ ነው ። ይህ ጋብቻ እኛ በማናውቀው እግዚአብሔር በሚያውቀው ተፈጽሟል ።

በዛሬው ጢት ሁለቱ ሙሽሮች በምእመናን መካከል በቅዱስ መሠውያው ፊት ራሳቸውን ዝቅ አድርገው እስከ ጊዜ ሞታቸው ድረስ እየተረዳዱ ለመኖር ቃል ኪዳን ገብተዋል።እግዚአብሔር አምላክ ወንዱን ሙሽራ ከምዕራብ አፍሪካ ሴቷን ሙሽሪት ከምሥራቅ አፍሪካ በአንድ ላይ አገናኝቶ በጋብቻ እንዲዋሐዱ አድርጓል ። ስለዚህ ከዚህ ቅዱስ ጋብቻ እግዚአብሔርን የሚፈራ ለሀገሩና ለወገኑ የሚጠቅም ቤተሰብእ እንዲገኝበት ሁላችን ወደፈጣሪያችን እንጸል

ተከታዩ ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



# የቤተሰብ ዐምድ

## ከብቸኛነት ወደ ቤተ ሰብነት

‘‘ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም ፣ ስለዚህም የምትስማማውን ረዳት እንፍጠርለት’’ ተብሎ የተነገረው ቃል ለዘርአ አዳም ቤተሰባዊ ኑሮ እንደመሠረት ድንጋይ ሆኖ የሚቆጠር ነው ።

ተከታዩም የቤተሰባዊ ኑሮ መዋቅር ጋብቻ ሲሆን እርሱም በጾታ ሁለት በአሳብና ከሥርዓተ ኑሮ በሚገኘው የመተሳሰብና የመረዳዳት ተግባር ግን አንድ አካል በሚሆኑ ባልና ሚስት አማካይነት የሚመሠረት ነው ። ዛሬ መላውን ዓለም እንደማዕበል ሞገድ አጥለቅልቆት የሚገኝ በቢሊዮን የሚቆጠረው ኅብረተሰብ ሁሉ የአንድ ቤተሰብ ውጤት መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል ስለዚህም ኅብረተሰቡ ራሱ የብዙ ቤተሰብ ድምር ነው ሲሉ ሊቃውንት ይናገራሉ ።

ይህ ከሆነ የመጀመሪያው ቤተሰብ አመሠራረት እንዴት ነበር? ብለን መጠየቅ ሊያስፈልግ ነው ። የዚህንም ጥያቄ መልስ የሚነግረን ቅዱስ መጽሐፍ የመጀመሪያው ቤተሰባዊ ኑሮ መሥራቾች ስለነበሩት ስለ አዳምና ሔዋን ጋብቻ የተሰጠ አምላካዊ መመሪያ ‘‘ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ። ከሚስቱም ጋር አንድ አካል ይሆናል ። (ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ) ። የሚል ነበር ። ይህም አባባል የሚያስረዳን ጋብቻ መመሥረት የሚችለው በሁለት ባልና ሚስት ብቻ መሆኑን ነው ።

እንግዲህ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ጋብቻ አመሠራረት ፩ኛ ከሴትም ከወንድም በኩል ምንም ዓይነት አሻሚ ምርጫ የሌለበት ፣

፪ኛ/ የጋብቻ ጥሎሽ ችግር ያልነበረበት ፣

፫ኛ/ የሠርግ ድግስ ችግርና ሐሳብ የሌለበትና እነማንን ጠርቼ እነማንን ልተው? የሚያሰኝ የኀሊና ወቀሳ ገና ያልተፀነሰበት ዘመን ስለነበር አዳምና ሔዋን በቀላሉ ተወጥተውታል።

በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ ሁሉ ችግር ዓይኑን አፍጦ ጥርሱን አግጦ በመታየቱ ወንዱንም ሆነ ሴቷን የብቸኛነት ኑሮ እንዳይጠናወተው ያሰጋል ። መፍትሔውስ? ከሚከተለው ጽሑፍ አጭር መልስ የሚገኝ ይመስላል ።

፩ኛ/ የጥሎሽ ጉዳይ

ከጥንት የምናውቀው የሙሽራ ጥሎሽ ፣ ኩታ ቀሚስ ጥላ መቀነትና ሻሽ ፣ ብር ቀለበት ሰጥቶ በብር ጉትቻ ፣ በሀብትሽ በሀብቴ (ላም አለሽ ወይ በሬ) በሚል አቻ ላቻ ፣ ሲፈጸም ነበረ ሕጋዊ ጋብቻ ።

ከጊዜ በኋላ ትውልዱ ምን ሆነ ፣ ይህ ዓይነት የአገር ባህል እየመነመነ የውጭ ወፍ ዘራሽ ባህል በቦታው ገነነ ፣ ጋብቻም መልክ አጥቶ መነገጃ ሆነ ።

በአንዳንድ ብሔረሰብ ሴት ልጅ የወለደ፡ በወርቅ ነገደ ይባላል አፍ ቃሪነት ቀርቶ ፈረንጆች ነን ያሉ ፡ ሴቶች በልጅነት ሲዳሩ ሲኳሉ ፣ የእጅ ወርቅ አምባርና የአንገት ወርቅ ሐብሉ ከጣት ቀለበት ጋር የጆሮ እንጥልጥሉ፣ ከልብስ ዓይነት በዓይን የሚያዩትን ሁሉ ፣ አጋትለው አጋብሰው ቁም ሣጥኑን ካልሞሉ ፣ ዕጮኞቻቸውን ችግር ላይ ሳይጥሉ ፣ ፍቅር አይገዛቸውም እንዲህ በቀላሉ ፣ የተንዛዛ የሠርግ ድግስ ብዛት ። የጋብቻ መቅሠፍት ከባህሉ ከልምዱ ከተራውም አንፃር፣ ለቀለበት በዓል ለቃል ማሠሪያው ክብር ፣ በተንዛዛ ድግስ ጠጥቶ መሣከር ፣ ጥቅም አላስገኝም ከድካም በስተቀር ፣ ጮማ እየቆረጠ በሻምባኝ ቢታጠብ ፡ በዊስኪ ተራጭቶ ሰክሮ ቢንተባተብ ፣ ፊልተር ጠጁ ቢራው ያለገደብ ቢዘንብ ሕዝብ አዳም ተነክሮ በአረቄ ቢጠመቅ ለአሞራ የሚተርፍ ያ ሁሉ ድግስ ሲያልቅ ፡ ምስጋናው ተረስቶ ቀርቶ ምርቃቱ መተማማት ብቻ ይሆናል ውጤቱ ።

ያም ሁሉ ሽርጉድ የዘፈን ጋጋታ ፣
ያ ሁሉ ጭፈራ እልልታና ሆታ ፡
ለቅጽበት ብቻ ነው ለአንዲት ቀን
ለአንድ አፍታ ፣
ተረስቶ ይቀራል እንደ ውሃ ሽታ ።
ከዚህ የተነሣ እንደተረዳነው
በገዛ ድግሱ ከሚደነቅ ይልቅ
ከሚመሰገነው
ይበልጣል ስሞታ ትችት ያሰለቸው ።
የሐሜቱም ሰበብ ግልጥ ነው ምሥጢሩ
እነእከሌን ጠርቶ እነ እከሌ ቀሩ ።
አሳላፊዎቹም ምንም ሳያዳሉ
ለእነከሌ ሰጥተው እከሌን ዘለሉ
እያሉ መሸርደድ ተለምዷል ከባህሉ ።
ታዲያ ይህን ስንል ዋናው ዓላማችን
ሠርግ እንዳይደገሥ ማከላከል ሳይሆን።
ነገ አዲስ ቤት ኅብረት ለሚመሠርቱ
የተንዛዛ ድግስ አማካይ ውጤቱ ።
ኋላ እንደሚያመዝን ከጥቅሙ ጉዳቱ
ለመጠቆም እንጂ አይደለም ለከንቱ ።
በዕቃ ግዢ ስም ከባንክ ተበድረው
ወይ እምነት በማጉደል የሕዝብ ካዝና
አራቁተው
ለጋሶች ለመምሰል ደግሰው ያበሉ
እንደ አረም ሲያንቃቸው ችግር
በመሐሉ
ልጆች ያሳድጉ ወይ ዕዳ ይከፈሉ ?
መክፈል አቅቷቸው ታሠሩም ቢባሉ
ከድግሱ አጨራሽ ካጨብጫቢው ሁሉ
ለአንዲት ቀን የሚሆን ዋስ እንኳ
ያጣሉ ።
በዚሁ ዓይነት ሒደት ሁሉን
ብታስተውሉ
እስካልተገረዘ ልምዱም ሆነ ባህሉ
አሳሳች ነውና ከሙሉ በክፍሉ
እስኪ እባካችሁ እንዳትታለሉ ።
ታላቁ ኢትዮጵያዊ ደራሲ አቶ ከበደ
ሚካኤልም የልማድን መምህርነት
ሲገልጡ
ምን ያህል ብርቱ ነው ኃይለኛ ጠንካራ
ልማድ የሁሉ ምንጭ ያገር የመከራ
ቂሙ እማይነቀል መርዙ የማይጠፋ
ምን ነገር ይገኛል ከልማድ የከፋ

ተከታዩ ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ዕረፍት

አቶ ምትኩ ለማ ከአባታቸው አቶ ለማና ከእናታቸው ወ/ሮ ፋንታዬ አዲስ አበባ ከተማ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ተወለዱ ዕድሚያቸው ለትምህርት ሲደርስ እግዚአብሔርን መፍራት አባትና እናትን ማክበር ለሕግ መታዘዝን እየተማሩ በወላጆቻቸው ቤት በሥነ ሥርዓት አደጉ ጥረህ ግረህ በግንባርህ ወዝ ብላ ተብሎ በታዘዘው መሠረት አቶ ምትኩ ለማም ልብስ ወደሚሰፉበት ማሠልጠኛ ገብተው በልብስ ስፌት ሙያ በሚገባ ሠልጥነው በዚሁ ተግባረ ዕድ ሥራቸውን ቀጥለዋል አቶ ምትኩ ለማ ዕድሚያቸው ለአቅመ አዳም ሲደርስ በሕግና በሥርዓት ሚስት አግብተው ስድስት ወንዶችና አንዲት ሴት ልጅ በጠቅላላው ሰባት ልጆችን ወልደዋል ። እነርሱም ግማሾቹ በሥራ ተቀጥረው ሀገራቸውንና ወገናቸውን በማገልገል ላይ ሲገኙ የቀሩት ደግሞ በትምህርት ላይ ናቸው።

አቶ ምትኩ ለማ ከ፲፱፻፵፰ ዓ.ም ጀምሮ በሞት እስከ ተለዩበት ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ድረስ በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በልብስ ተከህኖ ስፌት ተቀጥረው ፲፯ ዓመት በቅን መንፈስ አገልግለዋል አሁንም በማገልገል ላይ ሳሉ ከቅርብ ቀን ጀምሮ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት በሐኪም ሲረዱ ቆይተው መስከረም ፳፬ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ። ቀብራቸውም በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል ።

በቀብራቸውም ላይ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ሊቃውንት የጠ/ ቤተ ክህነት የመምሪያ ሐላፊዎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምእመናን ተገኝተዋል ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምድረ ሱዳን ሊቀ ጳጳስና የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተ/ ዋና ጸሐፊ ብፁዕ አቡነ ገሪማ በቀብሩ መጨረሻ ላይ ምዕራገ ጸሎት ሲያደርጉ ለሰዎች ሞት የማይቀር የተፈ



አቶ ምትኩ ለማ እኒህ ነበሩ

ጥሮ ግዴታ መሆኑን አስገንዝበው ማልቀስ እንባንም ማፍሰስ አብሮ ለኖረ ሰው ፣ አብሮ ለበላና ለጠጣ ሰው ፣ አብሮ ለተጫወተ ሰው ተገቢ መሆኑን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚወደው አልዓዛር ማልቀሱን ለማስረጃ ጠቅሰው ፊትን እየነጩ ደረትን እየደበደቡ እየወደቁና እየተነሡ ማልቀስ ተገቢ አለመሆኑን ተናግረዋል ።

ብፁዕነታቸው ትልቁ ቁም ነገር በሕይወተ ሥጋ ሳሉ መረዳዳቱ መተዛዘኑ ሲሆን ሌላው ደግሞ የሟቹን ቤተ ሰብእ መርዳቱ ነውና ሁሉም ሕዝበ ክርስቲያን በሕይወተ ሥጋ እየተረዳዱ ኑረው ሲሞት ደረትን ሳይደበድቡ ፊትን ሳይነጩ እንባን ብቻ በማፍሰስ ሙቱን መሸኘቱ ተገቢ መሆኑን አሳስበዋል ።

አቶ ምትኩ ለማ እግዚአብሔርን ፈሪ ሰውን አክባሪ ትንንሾቹን እንደ ልጆቻቸው ታላላቆችን እንደ እህቶቻቸውና እንደ ወንድሞቻቸው ሽማግሌዎችንና ባልቴቶችን እንደ አባታቸውና እንደ እናታቸው የሚወዱና የሚያከብሩ ደግና ርኅሩህ ሰው ነበሩ ።

ይሁን እንጂ ምንም ደግ ቢሆኑ ሞት ሥጋ ለለበሰ ሁሉ የማይቀር ዕዳ በመሆኑ አቶ ምትኩ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል አቶ ምትኩ ቤተ ክርስቲያናችን በቅን መንፈስ ያገለገሉ በመሆናቸው ለነፍሳቸው መንግሥተ ሰማያትን እንዲያወርሳት ለቤተ ሰቦቻቸውም መጽናናትን እንዲሰጣቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ወደ እግዚአብሔር ትማፀናለች ።

ከመንበረ ፀባዕት ቅ.ሥ.ካ. ጽ/ቤት

---

# ...በጸሎተ ተክሊል ተፈጸመ

ከገጽ ፳ የዞረ

ያለን በማለት ምዕራገ ጸሎት አድርገው የግብዣው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል ።

መጋባት በሁሉም ዘንድ የከበረ ነው ተብሎ እንደተጻፈው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በምታዝዘው መሠረት በጸሎተ ተክሊል ተጋብቶ በፍቅር እየተረዳዱ መኖር አምላካዊ ትእዛዝ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ያላመነ ባል ያላት ሚስት ብትኖር ይህ ከእርሷ ጋር ሊቀመጥ ቢስማማ አትተወው ያላመነ ባል በሚስቱ ተቀድሷልና ካለ በኋላ አንቺ ሴት ባልሽን ታድኚው እንደሆንሽ ምን ታውቂያለሽ ? በማለት ተናግሯል ። ፩ኛ ቆሮ ፯. ፲፫.፲፮ ።

እንደዚህ ያለው የተቀደሰ ጋብቻ በወ/ት ሳባ ታደሰ ብቻ ማክተም አይኖርበትም ሌሎችንም እርሷን የመሳሰሉ ክርስቲያኖቹ በመንፈሳዊ ፍቅር ወደ ክርስቶስ እንዲቀርቡ ቤተ ክርስቲያና ችን ትፈልጋለች ።

የዜናው አቅራቢ ቀ. ልሣነወርቅ በዛብህ



# የጤና ዐምድ

## የእናቶችና የሕፃናት ጤና አጠባበቅ

እናቶችና ሕፃናት የኅብረተሰብ ክፍሎች እንደመሆናቸው መጠን ባላቸው የተፈጥሮ ጠባይ ማለትም ደግሞ እርግዝና ፡ መውለድና የመሳሰሉት ለበሽታ ከዚያም አልፎ ለሞት በቀላሉ ሊጋለጡ የሚችሉ ናቸው ። ስለሆነም ከሌላው ሰው ይበልጥ በተለይ በጤና በኩል የተለየ እንክብካቤና ጥንቃቄ እንዲደረግላቸው ያስፈልጋል።በእናቶችና በሕፃናት መካከል ያለውን የሚታዩትን የጤና ችግር ብንመለከት ሕፃናት ከመወለዳቸው በፊት በእናታቸው ማኅፀን ውስጥ እንዳሉና ከተወለዱም በኋላ በቂ ምግብ ባለማግኘታቸው የአካባቢው ንጽሕና ባልተጠበቀበት ሁኔታ በማደጋቸው በምግብ ማነስና አለመመጣጠን እንዲሁም በተላላፊ በሽታዎች በተለይም እንደ ኩፍኝ ትክትክ የአንጀት ትላትሎች ተቅማጥና ለሌሎችም ለመሳሰሉት በሽታዎች ይጋለጣሉ ። በዚህ ምክንያት አብዛኛዎቹ ሕፃናት በጤና ጉድለት ሲሰቃዩ ብዙዎቹ በሕፃንነታቸው ይሞታሉ ።

እናቶችንም የወሰድን እንደሆን በመጀመሪያ ራሳቸው በቂ ምግብ ባለማግኘታቸው አቋማቸው የተጠናከረ ስላልሆነ በተጨማሪም ራስ በራስ በመወለዳቸውና በወሊድም ጊዜ በሠለጠኑ አዋላጆች ካለመረዳታቸው የተነሳ ብዙ ሥቃይ ይደርስባቸዋል እስከ መሞትም የሚደርሱት ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም ።

በገጠር ከሚኖረው ሕዝብ ከፍተኛ ድርሻ ያለባቸው ሴቶች ናቸው ይህም ከፍተኛ የሥራ ድርሻ ሴቶች በማርገዝ በመውለድና ከዚያም በላይ በማሳደግ ካለባቸው ሃላፊነት ጋር ሲጨመር ተገቢው ጥንቃቄ ካልተደረገላቸው ለከፍተኛ የጤና ችግር በቀላሉ የተጋለጡ ይሆናሉ ። ሕፃናትም እንደዚሁ ከመፀነሳቸው በፊት የእናታቸው ጤንነት የተሟላና የተጠናከረ ካልሆነ ከተፀነሱም በኋላ ከልዩ ልዩ በሽታዎችና አደጋዎች ካልተጠበቁ እንዲሁም አስፈላጊውን ጥሩ ምግብ ካልተሟላ ከዚያም ከተወለዱ በኋላ የሚገባቸውን ምግብ ካላገኙና ከበሽታም እንዲጠበቁ ካልተደረገ ለማደግ ያላቸው ዕድል በጣም የመነመነ ነው ።

በምግብ በኩል ያለውን የወሰድን እንደሆነ ሕፃናት እስከ አራት ወር ድረስ የእናታቸውን ጡት እንዲጠቡ ሆኖ ከዚያ ጀምሮ ገንቢና አልሚ ምግቦችን ኀይል ሰጪና ቪታሚኖችን እንዲያገኙ ማድረግ አስፈላጊ ነው ይህ ሲባል እንደ ወተት ፡ አትክልት ፡ ፍራፍሬ ቅጠላቅጠል የእህል ዘር ጥራጥሬ ድንች እንቁላልና የመሳሰሉት በዕድሜያቸው ልክ ተመጥኖ በመዘጋጀት እየቀያየሩ መመገብ ያስፈልጋል ። ታዳጊ የሆነው የሕፃናት ሰውነት የሚያስፈልገውን ምግብ እንዲያገኝ ማድረግ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው ። ከዚህም በላይ ወቅቱን በመጠበቅ ሕፃናት ለበሽታ መከላከያ ክትባቶችን እንዲያገኙ ማድረግ በጣም ያስፈልጋል ሕፃናት በቂ ምግብ ሳያገኙና ከበሽታ ሳይጠበቁ ቢያድጉ የሰውነታቸውና የአንጎላቸው ማደግ አጥጋቢ ስለማይሆን ብዙም የሚመኩባቸው አይሆኑም ስለዚህ

ሀ/ የእናቶችና ሕፃናት ቁጥር ከጠቅላላው ሕዝብ ወደ ሰባ በመቶ ያህሉ በመሆኑ

ለ/ በእናቶችና ሕፃናት መካከል ያሉት የጤና ችግሮች አብዛኛዎቹ ለመከላከል የማይቻሉ በመሆናቸው ።

ሐ/ ሕፃናት የወደፊት የሕብረተሰቡ ተረካቢዎችና አለኝታዎች በመሆናቸው ለእናቶችና ሕፃናት ጤና አጠባበቅ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ።

፩ኛ / ከእርግዝና በፊት የሰውነት እድገትና ለአካል መጠን መድረስ

ሕፃናት ከተወለዱ በኋላ አስፈላጊውን ምግብ ካገኙ አጥንታቸው ፡ ጡንቻዎቻቸው ፡ አንጎላቸውና እንዲሁም ልዩ ልዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው ያድጉና ጎልምሰው ከተወሰነ ቁመታቸው ልክ ይደርሳሉ ሆኖም ይህ በሚሆንበት ጊዜ የሚታዩ ልዩ ልዩ የአካል ለውጦች አሉ ።

ሀ/ በወንዶች ላይ የሚታዩ የአካል ለውጦች

ወንዶች ከተወለዱ ጀምሮ እስከ ፲፫ ዓመት ገደማ ድረስ ተገቢውን ምግብ በማግኘት ያድጋሉ ከዚያም በኋላ የአእምሮና የሰውነት ለውጦች ይታያሉ ይህም የድምጽ መጎርነን ከብብትና ከብልት አካባቢ ፀጉር መብቀልና ማደግ የጉሮሮ አጥንት ወይንም የማንቁርት ማደግና መጠንከር እንዲሁም የዘር ፍሬ መፈጠርና መብዛት ናቸው ። በአብዛኛዎቹ ወንዶች የዘር ፍሬ መፈጠር ማደግና መብዛት በአሥራ አምስት ዓመት ገደማ የሚጀምር በመሆኑ ከዚህ ዕድሜ በኋላ ወንዶች ከሴቶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ቢያደርጉ ፅንስ ለመፍጠር ይችላሉ ። ከአሥራ አምስት ዓመት በኋላ ጀምሮ ጺም በፊት ላይ መውጣት ይጀምርና የወንድነት ምልክቶች በሙላ በደንብ ተለይተው ይታያሉ ።

ለ/ በሴቶች ላይ የሚታዩ የአካል ለውጦች

ሴቶች ከተወለዱ ጀምሮ እስከ ፲ ዓመት ዕድሜ ምንም ያህል የሰውነት ለውጥ ሳይታይባቸው ያድጋሉ ወደ ፲፪ና ፲፫ ዓመት ላይ ጡቶቻቸው ማጎጥጎጥ ይጀምራሉ ድምፅ ይቀጥናል ዳሌ ይሰፋና ወገብ ቀጠን ይላል በ፲፫ና ፲፬ ዓመት ላይ ፀጉር ከራስ ላይ በስተቀር በብብት ውስጥና በብልት አካባቢ መብቀል ይጀምራ



www.ethiopianorthodox.org

ል ከዚህም በስተቀር በዚህ ዕድሜ አካባቢ በሴትም የአካልና የአእምሮ ለውጦች ይታያሉ ። በሴት ልጅ የማህፀን አጥንት ውስጥ የታቀፉ የዘር አካሎች ኣኗቸው እነዚህም በሚሊዮን የሚቆጠሩ የዘር ፍሬ የያዙ ዕንቁላሎች ማመንጫ ዕጢዎች ከግራና ከቀኝ በኩል ሲኖሩ የሴት የዘር ፍሬ ወይም ዕንቁላል የሚያልፍባቸው ቧንቧዎች ማኅፀን አፍና የሴት ብልትን ይይዛል ።

የወር አበባ መታየት

ማንኛውም ሴት ልጅ ፲፫ና ፲፬ ዓመት ገደማ የዘር ፍሬ ወይም ዕንቀላል ያድግና በመብሰል ማመንጫ ዕጢዎች ተገንጥሎ በቧንቧው ውስጥ አድርጎ በማኅፀን በኩል ወደ ውጭ ያልፋል ።ይህ የሚሆነው በአብዛኛዎቹ ሴቶች በየወሩ ሲሆን በጥቂቶች ደግሞ ከወር ባነሰ ወይም በበለጠ ጊዜ ይሆናል የዘሩ ፍሬ ወይም ዕንቁላል አንድ ጊዜ ከግራ ቀጥሎም ከቀኝ በመፈራረቅ እያደገ የሚመጣው ሲሆን አልፎ አልፎም ከሁለቱም በኩል አንድ ላይ ይወጣል ። የዘሩ ፍሬ አድጎና በስሎ ከዕንቁላሉ ማመንጫ ዕጢ ተገንጥሎ በቧንቧዎቹ አድርጎ በማኅፀን በኩል ወደ ውጭ ይወጣል ይህም ሲሆን ማኅፀን ወሩን ሙሉ ፅንስ ይፈጥራል በሚል ለፅንሱ ምግብ ይሆናል በማለት ያዘጋጀውን የደም መደብ የዘሩ ፍሬ ሲያልፍ እየጨመቀ ደም መፍሰስ ይጀምራል ይህም ከ፬ - ፯ ቀን ይቆይና ደም መፍሰሱ ያቆማል ። ይህ የወር አበባ ወይም አደፍ ተብሎ ይጠራል እንግዲህ የወር አበባ የሚታየው ከወንድ ዘር ፍሬ ያልተገናኙ ዕንቁላል ከማህፀን ሲወገድ ነው የወር አበባ በአብዛኛዎች ሴቶች በየወሩ የሚሆን ሁኔታ ቢሆንም በጥቂቶች ከሦስት ሳምንት እስከ አምስት ሳምንት ባለው ጊዜ ሊሆን ይችላል ።

በወር አበባ ጊዜ የሚደረጉ ጥንቃቄዎች

አንዲት ሴት የወር አበባ በምታይበት ጊዜ ማኅፀኑ ደሙን ለማፍሰስ ሲጨምቅ የሆድ ቁርጠትና የወገብ መከትከት ይሰማታል ለዚህ እንደመፍትሔ የሚረዳ ቀላል ሰውነትን የሚያሞቅ ሥራን መሥራት ትኩስ ነገሮችን መጠጣት እግርን በሙቅ ውሃ መንከር የሙቅ ውሃ ላስቲክ በፎጣ ጠቅልሎ ከእምብርት በታች መያዝ ሲሆን ይህም የማያሽል ከሆነና ሕመሙ ከፍተኛ ከሆነ የሕክምና ዕርዳታ መሻት ያስፈልጋል። በወር አበባ ጊዜ ሊላ መወሰድ ያለበት ጥንቃቄ

በተለይ የግል ንጽሕናን በሚመለከት ነው አንዲት ሴት በወር አበባዋ ጊዜ ከሌላው ጊዜ የበለጠ የግል ንጽሕናዋን መጠበቅ ይኖርባታል በየቀኑ ሰውነቷን ለብ ባለ ውሃ መታጠብ አለባት ።

የፅንስ መፈጠር

የዘሩ ፍሬ አድጎና በስሎ ከእንቁላሉ ማመንጫ ዕጢ ተገንጥሎ በቧንቧው አድርጎ [illegible] ጣበት ሰሞን ሴትዋ ልጅ ከወንድ [illegible] የግብረ ሥጋ ግንኙነት ብታደርግ [illegible] የወንዱ የዘር ፍሬ ተገናኝተው [illegible] ይፈጥራሉ ከዚያም ፅንሱ በተዘጋጀለት የማኅፀን የደም መደብ ውስጥ በመቀመጥ እየተመገበ ያድጋል ። ከዚያም በእንግዲህ ልጅ አማካኝነት ፅንሱ የሚያስ ፈልገውን ምግብ ከእናቱ እየወሰደ ለዘጠኝ ወራት ያህል ቆይቶ ይወለደል ፅንስ ከተፈጠረ በኋላ ያለው የደም መደብ ለፅንሱ ምግብ ስለሚሆን እርግዝና እንደጀመረ የወር አበባ መታየት ያቆማል ከዚያም ሕፃኑ ከተወለደ በኋላ ጥቂት ወራት ቆይቶ እንደገና እንደቀድሞው በየወሩ መታየት ይጀምራል እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን የወር አበባ መታየት ጤናማ የሰውነት ጠባይ ነው እንጅ በአንዳንዶችእንደሚታመነው ሴት ልጅ በኃጢአትዋ ወይም በመባለግ የምታመጣው ነገር አለመሆኑ ለማንም ግልጽ ሆኖ መታወቅ አለበት ። ሴት ልጅ የወር አበባዋን ማየት ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ለአቅመ ሔዋን ደርሳለች ይባላል ። ይህም ማለት ከወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ብታደርግ ፅንስ ሊፈጠር ይችላል ማለት ነው ሆኖም ፅንስ እንዳይፈጠር ከፈለገች የወር አበባዋ እንደጀመረ ከዚያም ፀድታ እስከ አምስት ቀን ድረስ እንዲሁም የሚቀጥለው የወር አበባዋ ሊመጣ አምስት ቀን ያህል ሲቀረው ባለው ጊዜ ብቻ ከወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በማድረግ ፅንስ እንዳይፈጠር ለመከላከል ትችላለች በሌላ በኩል ደግሞ መውለድ የምትፈልግ ከሆነ ከወር አበባዋ ከጸዳች ከአምስት ቀን በኋላ ጀምሮ የሚቀጥለው የወር አበባዋ እስከ መጣ አምስትቀን ያህል እስኪቀረው ባለው ጊዜ ውስጥ ከወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በማድረግ ለመጸነስ ትችላለች ምክንያቱም ይህ ጊዜ የዘሩ ፍሬ አድጎና በስሎ ከዕንቁላሉ መመንጫ ዕጢ ተገንጥሎ ሊወጣ የሚችልበት ጊዜ በመሆኑ ነው ።

ከላይ የተጠቀሰው ለመውለድ ወይም ላለመውለድ የሚደረገው ጥንቃቄ ለአብዛኛዎቹ ሴቶች የሚጠቅም ሲሆን አልፎ አልፎ ለአንዳንድ ሴቶች በልዩ ልዩ ምክንያት ላይሠራ ይችላል ። የወር አበባን በመከታተል የግብረ ሥጋ ግንኙነት ቢያደርጉም አንድ አንድ ጊዜ በልዩ ልዩ በተፈጥሮም ሆነ በወንዱ ወይንም በሴትዋ ህመም ምክንያት ለማርገዝ አይቻልም ይሆናል አንዳንድ ችግር በህክምና ዕርዳታ ሊወገድ ስለሚችል የመሀንነት ችግር ያለባቸው ቤተሰቦች የሕክምና ዕርዳታ መሻት ሊጠቅማቸው ይቻላል ።

## የቤተ ሰብ ዓምድ

ከገጽ ፳፪ የዞረ

በማለት ጽፈው እንደነበር ይታወሳል ።

ስለዚህ ጋብቻን ያህል የኅብረተሰብ ዋልታና ምሰሦ በጽኑ መሠረት ላይ መገንባት ሲገባ በሰው ሠራሽ የልማድ ትብትብ ብዛት መሥመሩን እንዲለቅ ከማድረግ መጠበቅ ይቻል ዘንድ ልንመክርበት ይገባል ።

ቁ/ መክብብ አጥናው



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዛመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ሰባት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቁ. 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. [illegible]
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org